# ሕፃናትና ሕግ በኢትዮጵያ
# የተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መብቶች ድንጋጌ ጉዳይ*

በጥላሁን ተሾመ**

> ሕፃናት በአካል ብቃትና በአእምሮ ብስለት ገና ጮርቃዎች ስለሆኑ ከልደት በፊትም ሆነ በኋላ ልዩ ጥበቃና ክብካቤን የሻሉ፣ ይህም ተገቢውን የሕግ ድጋፍ ሊያገኝ ይገባል… ምርጥ ምርጡን ለህፃናት መስጠት የሰው ልጆች ሁሉ ግዴታ ነው።[1]

## 1· *መግቢያ*

የሕፃንነት ዘመናት እያልን በምንጠራቸው የመጀመርያዎቹ አመታት የሰው ልጅ ደካማና የሌሎች ወገኖቹን ያልተቆጠበ እርዳታ የሚሻ ፍጡር ነው። ይህ ነባራዊ እውነታ ነው ለህፃናት ልዩ ክብካቤና ጥበቃ እንድናደርግላቸው ግድ የሚለን። ሕፃናት የተሟላ ስብዕናን ይዘው ያድጉ ዘንድ ፍቅርና ደስታን በተላበሰ አካባቢ ማደግ ያስፈልጋቸዋል።

ይህ ለሕፃናት ልዩ ጥበቃንና ክብካቤን የማድረግ ሀላፊነት ከሁሉም አስቀድሞ የወላጆችና የቅርብ ቤተሰቦች ግዴታ መሆኑ የሚያነጋግር አይደለም። ያም ሆኖ የሕፃናት አካላዊና መንፈሳዊ ዕድገት በሚያልፍባቸው ረዥም አመታት ሕብረተሰብና መንግሥትም የየበኩላቸውን እገዛና ድጋፍ የማበርከት ሃላፊነት አለባቸው። ብርቅና ድንቅ ፍጡራን በመሆናቸው ልባችን ለሕፃናት ይራራል፣ ለእነሱ ያለብን ግዴታም ከሁሉም በላይ የጠነከረ ነገር ግን ከሁሉም የጣፈጠ ነው።

ከዚህ መሠረታዊ ሀሳብ በመነሳት ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግ ከያዝነው ሃያኛው መቶ ምዕተ ዓመት መባቻ ጀምሮ ሕፃናትን · የሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ የዓለም አቀፍ የመንግሥታት ሕግ አካላት ይሆኑ ዘንድ የተለያዩ ገንቢ እርምጃችን ሲወስድ ተስተውሏል። እ·ኤ·አ· በ1924 በጄኔቫ ይፋ በተደረገው የሕፃናት መብቶች መግለጫ ውስጥ ዕውቅና ያገኙት የሕግ ግዕዛት፣ የሕፃንነት ዘመን ልዩ ክብካቤን የሚሻ መሆኑ የተገለጸበት እ·ኤ·አ· በ1948 የወጣው የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 25፣ እ·ኤ·አ· በ1959 በተባበሩት መንግሥታት አማካይነት በታወጀው የሕፃናት መብቶች መግለጫ የሠፈሩት አሥር መሠረታዊ ነጥቦች፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ያወጃቸው ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ድንጋጌ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ መብቶች ድንጋጌ ያካተቱዋቸው የህፃናትን መብቶች የሚመለከቱ ፍሬ ነገሮች ሁሉ አንድ ወጥ የሆኑና ተከታታይነት ያላቸው የሕግ ግዕዘትን በመቅረጽ ረገድ ዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ እየተጓዘበት ያለውን አቅጣጫ የሚጠቁሙ ናቸው። እ·ኤ·አ·

---

* ይህ ጽሁፍ ለየት ባለ ዝግጅት ለመጀመርያ ጊዜ የቀረበው ሬድ ባርና ኢትዮጵያ በሀገራችን ሥራውን የጀመረበትን 25ኛ ዓመት ለማክበር እ·ኤ·አ· ኦክቶበር 8 ቀን 1994 አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ባካሄደው አውደ ጥናት ላይ ነበር። በእንግሊዝኛ ቋንቋ የነበረው የጽሁፉ ርዕስም "The Situation of Ethiopian Children in the Context of the United Nations Convention on the Rights of the Child" የሚል ነበር። ይሁንና ይህኛው ጽሁፍ ከዚያ በኋላ በወጡ ሕግጋትና የፖሊሲ ሰነዶች እንዲዳብር ሆኗል።

** ተባባሪ ፕሮፌሰርና ዲን፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሕግ ፋክልቲ፣ ቀደም ሲል የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ የነበሩ።

1 እ·ኤ·አ· በ1959 ይፋ ከተደረገው የሕፃናት መብቶች መግለጫ መግቢያ የተወሰደ፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ እ·ኤ·አ· ኖቬምበር 20 ቀን 1959 ባደረገው ስብሰባ በወሰኔ ቁጥር 1386 (XIV) የታወጀ፣ "Human Rights, A Compilation of International Instruments" በተባለውና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ መብት ማዕከል የበላይ ጠባቂነት እየታተመ በሚወጣው መጽሐፍ አንደኛ ቮልዩም ክፍል አንድ ውስጥ እ·ኤ·አ· በ1993 ታትሞ የወጣ፣ ጄኔቫና ኒውዮርክ፣

በ1989 በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የወጣው የህፃናት መብቶች ድንጋጌም የዚህ ጥረት ውጤት ነው።[2]

ይህ ድንጋጌ በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የሕግ አውጭ አካል[3] በአዋጅ ቁጥር 10/1984 እንዲጸድቅ ተደርጓል። በአዋጁ አንቀጽ 4 መሠረትም አዋጁ ሥራ ላይ የሚውለው ከጥር 22 ቀን 1985 ዓ.ም ጀምሮ ነው። ይህ የማጽደቂያ አዋጅ አጠቃቀስን፣ ማጽደቅን፣ የሥልጣን ውክልናንና ሥራ ላይ የሚውልበትን ጊዜ ብቻ የሚያመለክቱ አራት አናቅጽ ያሉት ነው። በሽግግሩ ወቅት ቻርተር[4] መሠረት ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ማጽደቅ የምክር ቤቱ ሥልጣን የነበረ በመሆኑ ድንጋጌው በአሁኑ ጊዜ የሀገሪቱ ሕግጋት አካል ሆኗል ብሎ መናገር ይቻላል።

የማጽደቂያ አዋጁ አንቀጽ 3 የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ለአዋጁ አፈጻጸም ተገቢ መስሎ የታየውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ሥልጣን ይሠጠዋል። የድንጋጌው ሙሉ ትርጉም በአማርኛ ቋንቋ[5] ተተርጉሞ በህፃናት፣ ወጣቶችና ቤተሰብ ጥበቃ ድርጅት አማካይነት ታትሟል።[6] በአፍሪካ ህፃናት ደህንነት ጥበቃና ጥቃት ተከላካይ ማኅበር የኢትዮጵያ ቅርንጫፍ እየተባለ የሚታወቀው መንግሥታዊ ያልሆነ ተቋምም ድንጋጌውን በሌሎች የሀገሪቱ ቋንቋዎች አስተርጉሞ አሳትሟል።

በድንጋጌው አንቀጽ 42 እንደተመለከተው ይህ ጥረት ድንጋጌውን በሕዝብ ዘንድ እንዲታወቅ በማድረግ ረገድ ገንቢ አስተዋፅኦ እንዳለው አይካድም።[7] ይሁንና የድንጋጌውን አናቅጽ አተረጓጎምና አፈጻጸም የሚመለከቱ ውዝግቦች በፍትሕ መድረክ በሚነሱበት ጊዜ አንዳንድ ችግሮች ሊከተሉ የሚችሉ መሆናቸውን ልብ ማለት ይገባል። ይህም ድንጋጌው በፌዴራሉም ሆነ በክልል መንግሥታት የሥራ ቋንቋዎች በይፋ ባለመተርጎሙ ምክንያት ሊነሳ የሚችል ችግር ነው። የድንጋጌው አናቅጽ ታትመው የወጡባቸው ጥራዞችም ይፋዊ የሆኑ መንግሥታዊ የሕግ ማውጫ ጋዜጦች አይደሉም። ከዚህም ሌላ የተለያዩ አካላት የሚያሳትሟቸው ትርጉሞች ልዩነት ሊታይባቸው ስለሚችል የትኛውን እንቀበል የሚለው ጥያቄም ራሱን የቻለ ችግር ነው።

---

2 እ.ኤ.አ. በኖቬምበር 20 ቀን 1989 በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ቁጥር 44/25 ተቀባይነት አግኝቶ አባል ሀገሮች ከፊርማቸው እንዲያጸድቁት ክፍት የተደረገ፣ እላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር1 በተገለጸው መጽሐፍ ታትሞ የወጣ፣ ከዚህ በኋላ "ድንጋጌው" እየተባለ የሚጠቀስ።

3 ይህ አካል "የተወካዮች ምክር ቤት" እየተባለ ይጠራ የነበረው ነው። የኢትዮጵያ ሽግግር ወቅት ቻርተር አንቀጽ ዘጠኝን ይመለከቷል፤ ነጋሪት ጋዜጣ 50ኛ ዓመት ቁጥር 1። በአሁኑ ጊዜ ግን የሽግግሩ ዘመን መስተዳድር ያበቃ እንደመሆኑ መጠን ይህ ሕግ የማውጣት ሥል ጣን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽን ምክር ቤት እየተባሉ ለሚጠሩት የፌዴራሉ መንግሥት የሕግ አውጭ አካላት ተላልፏል። የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 53 እስከ 68 ይመልከቱ። /ከዚህ በኋላ "ሕገ መንግሥት" ተብሎ የሚጠቀስ። በነገራችን ላይ "ነጋሪት ጋዜጣ" ያ በኢትዮጵያ ውስጥ ይፋዊው የሕግ ጋዜጣ ነው። የነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋምያ አዋጅ ቁጥር 1/1934 ይመለከቷል። ከ1988 ዓ.ም ወዲህ ደግሞ ይኸው የጋዜጣው ስያሜ "ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ" በሚል ተለውጧል። የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988 ይመልከቱ።

4 የቻርተሩን አንቀጽ 9/ለ/ ይመለከቷል። በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55/2/ መሠረት በአሁኑ ጊዜ ይህ ሕግ የማውጣት ሥልጣን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሆኗል። ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ኢትዮጵያ ውስጥ የሚጸድቁበትን ሥርዓት በተመለከተ ደግሞ የዓለም አቀፍ ውሎች መዋዋያ ሥነሥርዓት አዋጅ ቁጥር 25/1980፣ ነጋሪት ጋዜጣ 48ኛ ዓመት ቁጥር 5 ይመልከቱ።

5 አማርኛ የፌዴራሉ መንግሥት የሥራ ቋንቋ ነው፤ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 5/2/ ይመለከቷል።

6 ይህ አካል በሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የበላይ ተቆጣጣሪነት የተዋቀረ ነገር ግን ራሱን ችሎ የሚንቀሳቀስ ተቋም ነው።

7 "አባል አገሮች የዚህን ኮንቬንሽን መርሆዎችና ድንጋጌዎች ለህፃናትም ሆነ ለአዋቂዎች ተገቢ በሆነ መንገድ በሰፊው ለማስተዋወቅ እርምጃ ይወስዳሉ።"

የዚህ ጽሁፍ ዐቢይ ዓላማ ግን ይህን የትርጉም ችግር መመርመር አይደለም። የጽሁፉ ዓላማ የሕፃናትን መብቶች በመጠበቅ ረገድ ጠቀሜታ ያላቸውን ሕግጋት በድንጋጌው ከተቀመጡት መስፈርት አኳያ መመልከት ነው። በመሆኑም አግባብ የሆኑ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት አናቅጽን ጨምሮ ዐበይት የሚባሉትን የሀገሪቱን ሕግጋት ለመመርመር ሙከራ ይደረጋል። እንደዚሁም በድንጋጌው የሠፈሩትን መሠረተ ጉዳዮች ለመተግበር ጠቀሜታ አላቸው የተባሉ ዋና ዋና ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና መዋቅራዊ ጉዳዮችም በመጠኑ ይዳሰሳሉ።

## 2· የድንጋጌው መሠረተ ሀሳቦችና ከኢትዮጵያ ሕግጋት ያላቸው መጣጣም፣

### 2·1· ትርጉም

በሕግ ቋንቋ ልጅ ወይም ህፃን የሚለው አነጋገር በሁለት መንገዶች ሊፈታ ይችላል። የመጀመሪያው በወላጆችና በተወላጆች መሀል ያለውን የሥጋ ዝምድና ለማሳየት ሥራ ላይ የሚውል ነው።[8] በሁለተኛው ትርጉም ደግሞ የሰውን ልጅ የመጀመሪያ የዕድሜ ዘመናት ለመግለጽ የምንጠቀምበት ነው።[9] ድንጋጌው የሚመለከተውም ይህንኑ ሁለተኛውን ትርጉሙን ነው። በድንጋጌው የመጀመሪያ አንቀጽ "ሕፃን" የሚለውን ቃል የሚተረጉመው "በሀገሩ ሕግ መሠረት ከዚህ ባነሰ ዕድሜ አካለ መጠን ካልደረሰ በቀር ዕድሜው ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው ነው" በማለት ነው። ይህ ዕድሜ አካለ መጠን የሚደርስበት ቢሆንም ድንጋጌው ከዚህም ያነሰ የዕድሜ ገደብን የሚያስቀምጡ የሕግ ሥርዓቶችንም ይቀበላል። በኢትዮጵያ ሕግ ህፃን የሚባለው "በሁለቱም ፆታ ዕድሜው ገና አሥራ ስምንት ዓመት ያልሞላው ሰው ነው።"[10] ይህ አጠቃላይ ደንብ የራሱ የሆኑ ልዩ ሁኔታዎች ስላሉት ሕጉ ለአንዳንድ ጉዳዮች ዝቀተኛ የዕድሜ ጣሪያዎችን ያስቀምጣል። በፍትሐ ብሔር ሕግ ይህ ሁኔታ ከሞግዚት አስተዳድር ነፃ መውጣት እየተባለ ይታወቃል። ለምሳሌም ያህል ዕድሜዋ አሥራ አምስት ዓመት የሆናት ልጃገረድ የጋብቻ ሥርዓትዋን ስትፈጽም ያለምንም ተጨማሪ ውጣ ውረድ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ትሆናለች። ከጋብቻ ጋር ባልተያያዙ ሁኔታዎችም ቢሆን አድራጎቱ የልጁን ጥቅም የሚያራምድ በሚሆንበት ጊዜ የቤተ ዘመድ ጉባኤ ዕድሜው አሥራ አምስት ዓመት የሞላውን ልጅ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ሊያወጣው ይችላል።[11] በዚህ መልክ አንድ ጊዜ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የወጣ ልጅ ለማንኛውም ጉዳይ ሁሉ እንደአዋቂ ተደርጎ ይገመታል። ለአብነት ያህል እንደዚህ ዓይነቱ ልጅ በመብት ደረጃ ከቤተሰቦቹ ቀለብ ሊጠይቅ አይችልም፣ አካለ መጠን አላደረስኩም በማለትም ያደረገውን ውለታ የማፍረስ ክርክር እንዲያነሳ ሕግ አይፈቅድለትም።[12]

---

8 ለምሳሌ ያህል የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥሮችን 550፣ 739 እስከ 741፡ 745/1/፣ እና 746 ይመልከቱ። አዋጅ ቁጥር 165/1952፣ ነጋሪት ጋዜጣ በተለይ የወጣ፣ 19ኛ ዓመት፡ ቁጥር 2፣ /ከዚህ በኋላ የፍ·ብ·ሕ· እየተባለ የሚጠቀስ።/

9 የፍ·ብ·ሕ·ቁ·2 እስከ 4፣ እንዲሁም አግባብ የሆኑትን የሕጉን አንደኛ መጽሐፍ፣ አንቀጽ 2፣ ምዕራፍ ሁለት ደንቦች ከዚህ ጋር ያገናዝቧል።

10 የፍ·ብ·ሕ·ቁ 198፣ ሕጉ "ህፃን" የሚለውን አነጋገር የሚያስቀምጠው "አካለ መጠን ያላደረሰ" በሚለው ሐረግ ነው።

11 የቤተ ዘመድ ጉባዔ አብዛኛውን ጊዜ የሚቋቋመው ከህፃኑ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች፣ አካለ መጠን ከደረሱ ወንድምና እህቶች በተውጣጣ አካል ነው። ጉባዔው ሕግ የህፃኑን መብት ለመጠበቅ ከሚሰይማቸው አካላት አንዱ ነው። የፍ·ብ·ሕ·ቁ 241 እና ተከታታዮቹን አናቅጽ ይመለከቷል። ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ መውጣትን በተመለከተ ደግሞ የዚህኑ ሕግ ቁጥሮች 329 እስከ 334 ይመልከቱ።

12 የፍ·ብ·ሕ·ቁ· 807,808 እና 812 /ቀለብን በተመለከተ/፣ ቁ· 313፣ 314፣ እና 1808 /ውል ማፍረስን በተመለከተ።/

በወንጀል ሕጎችም አሥራ አምስት የሞላቸው ልጆች ልክ እንደማንኛውም ሰው ለፈጸሙት ተግባር የወንጀል ሀላፊነት አለባቸው። ይህ የዕድሜ ክልል በሕጉ "አካለ መጠን ከማድረስ አስቀድሞ ያለው መካከለኛ ጊዜ" እየተባለ የሚታወቀው ነው።[13]

## 2·2· ሕፃናትን በእኩልነት ስለማየት

የድንጋጌው አንቀጽ 2 በዚህ ረገድ ያለውን የፈራሚ መንግሥታት ግዴታ ሲያስቀምጥ "በግዛታቸው ክልል የሚገኝ እያንዳንዱ ህፃን…ምንም ዓይነት መድልዎ ሳይደረግበት የመብቱ ተጠቃሚ እንዲሆን በዚህ ኮንቬንሽን የተመለከቱትን መብቶች ያከብራሉ፣ ተግባራዊነታቸውንም ያረጋግጣሉ።" በማለት ይደነግጋል።

ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያ ድንጋጌውንም ሆነ የተቀሩትን ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ሰነዶች[14] ከመቀበሏ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ የወጡትን ሕጎች ስንቃኝ ዘርን፣ የቆዳ ቀለምን፣ ፆታን፣ ቋንቋን፣ ፖለቲካዊም ሆነ ሌላ አመለካከትን፣ ብሔረሰብን፣ ኀሣን ወይም ማኅበራዊ ምንጭን መሠረት በማድረግ አድሎአዊ አሠራርን የሚሰብኩ

ሕግጋትን አናገኝም።[15] በፖሊሲ ደረጃም ቢሆን በዚህ ረገድ የተሠሩ ግልፅ ግድፈቶች አሉ ብሎ መናገር አይቻልም። እርግጥ በአንዳንድ ልማዳዊ አሠራርን ከረር አድርገው በሚተገብሩ አካባቢዎች ሀይማኖትን፣ ኀሣን ወይም ማኅበራዊ መሠረትን መነሻ በማድረግ ል ዩነት የሚያደርጉ ልምዶች አልፎ አልፎ ይስተዋላሉ። እነዚህም ቢሆኑ ታዲያ እስከዚህ ሥር የሠደዱ ሆነው የድንጋጌውን መርሆዎች ገቢራዊ አፈጻጸም የሚያውኩ አይደሉም፤ የሕግ ድጋፍም የላቸውም። "በዚህ በፍትሐ ብሔር ሕግ ውስጥ ለተመለከቱት ጉዳዮች ከዚህ በፊት በልማድ ወይም ተጽፈው ይሠራባቸው የነበሩት ደንቦች ሁሉ" ተሽረዋል የሚለው የሕጉ ቁጥር 3347/1/ ይህን በተመለከተ ለአብነት የሚጠቀስ ነው።

## 2·3· የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች

---

13 ፊሊፕ ግራቨን፣ ስለኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ መግቢያ ሕግ ፋኩልቲ፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ (1965 እ·ኤ·አ·) ገጽ 151 የትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 56፣ አዋጅ ቁጥር 158/47፣ነጋሪት ጋዜጣ በተለይ የወጣ፣ 16ኛ ዓመት ቁጥር 2፣ /ከዚህ በኋላ የው·መ·ሕ· እየተባለ የሚጠቀስ/፣ ይመልከቱ፣

14 ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሰነዶች የሚባሉት፣ /ሀ/ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ፣ /ለ/ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል [illegible] ተጨማሪ ሰነድ፣ እና /ሠ/ የሞት ፍርድን ቀሪ በማድረግ ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶችን የተቀበሉ ሀገሮች በፈቃደኝነት ብቻ ሊያከብሩት የሚገባ ሁለተኛው ተጨማሪ ሰነድ ናቸው። ከእነዚህ የመጀመርያዎቹ ሦስቱ በኢትዮጵያ መንግሥት በይፋ ታውቀው ተቀባይነት አግኝተዋል። የእነዚህን ሰነዶች ዝርዝር ለማየት እላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 1 የተገለጸውን ሥራ ገጽ 1 እስከ 50 ይመልከቱ።

15 የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 25 ይመለከቷል።

እንደሌሎች ሀገሮች ህፃናት ሁሉ የኢትዮጵያ ሕፃናትም በርካታ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች አሏቸው። ከሦስት አሥርተ ዓመታት በፊት ሥራ ላይ የዋሉት ብዙዎቹ የሀገሪቱ ሕጎች መሠረታዊ የሆኑ የሰብዓዊ መብት ጥበቃ መርሆዎችን በውስጣቸው ያካተቱ ናቸው። ከእነዚህ መብቶች ውስጥ፣ የመኖር ነፃ የመሆንና ያለመደፈር መብት፣ ከባርነትና ከግዳጅ ሥራ ነፃ የመሆን መብት፣ ከስቃይና ሰብዓዊ ክብርን አዋራጅ ከሆኑ ቅጣቶች የመጠበቅ መብት፣ በሕግ ፊት በእኩልነት የመታየት መብት፣ በተቃራኒው እስካልተረጋገጠ ድረስ እጥፊ ተብሎ ያለመገመት መብት፣ በግል ሕይወት ከሌሎች ጣልቃ ገብነት የመጠበቅ መብት፣ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። እንደገናም እነዚሁ መብቶች በ1987 በጸደቀው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥትም ዕውቅናን ያገኙ ናቸው።[16]

የድንጋጌው አንቀጽ 6፣ 12 እስከ 16፣ 35፣ እንዲሁም 37 እና 40፣ በእነዚህ መሠረታዊ መብቶች ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። ከአንቀጽ 12 እስከ 16 ያሉት ድንጋጌዎች የህፃናትን የሲቪል መብቶች ዘርዝረው ከማስቀመጣቸውም ባሻገር እንደዕድሜያቸው ደረጃና እንደአመለካከታቸው ብስለት ህፃናት የሚሠነዝሯቸው ሀሳቦች ዕውቅና ሊያገኙ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች ያስቀምጣሉ። ይህም በቤተሰብ፣ በፍትሕና አስተዳደር አካላት ዘንድ፣ በሥርዓተ ትምህርት ቀረጻና በትምህረት አሠጣጥ ተግባራዊ መሆን እንደሚገባውም ያስገነዝባሉ። የወላጆች የአሳዳጊነት ተግባርና ሀላፊነት እንተጠበቀ ሆኖ እነዚህ መብቶች ሕፃናት ማንኛውንም መረጃ ጠይቆ በማግኘት ሀሳባቸውን በነፃ በመግለጽ፣ በመረጡዋቸው ማኅበራት በመደራጀትና ሰላማዊ በሆኑ ህዝባዊ ስብሰባዎች በመሳተፍ ረገድ ሊኖሯቸው የሚገቡትን መብቶች ሁሉ ያካትታሉ።

የድንጋጌው አንቀጽ 14 ደግሞ ህፃናት ሊኖራቸው የሚገባውን የሀሳብ የሕሊናና የሃይማኖት ነፃነት የሚመለከት ነው። በዚህ አንቀጽ ውስጥ የሃሳብና የሕሊና ነፃነት ከሃይማኖት ነፃነት ጋር በእኩል ደረጃ እንዲቀመጡ የተደረገው "ምንም ዓይነት ሃይማኖትን ከማይከተል፣ ወይም እንደሰብዓዊነትና ሳይንሳዊ ቁስአካልነት ያሉ ዓለማዊ ፍልስፍናዎችን ብቻ ከሚቀበል ቤተሰብ" የሚመጡ ሕፃናትን መብት ለመጠበቅ ሲባል ነው።[17] በዚህ አሠራር፤ ድንጋጌው፣

1· ህፃናት በእነርሱ፣ በወላጆቻቸው ወይም በቤተሰቦቻቸው ሃይማኖትና አመለካከት ምክንያት ጥቃትና መድልዎ እንዳይደረግባቸው ይከላከላል፣

2· ህፃናት የራሳቸውን ሃይማኖትና አመለካከት በማጥናትም ሆነ በመስበክ ረገድ የአላቸውን መብት ይቀበላል፣ የሌሎችን እምነቶች ለመቀበል እንዳይገደዱም ይጠብቃቸዋል፣

3· ሃይማኖቶቻቸውን በተመለከተ በሚካሄዱ በማናቸውም በዓላትና የፀሎት ሥነ ሥርዓቶች ውስጥ ያላቸውን የመሳተፍ መብት ይጠብቃል፣

16 ለምሳሌ ያሕል የሰዎችን መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች የሚመለከቱትን የሕገ መንግሥቱ ምዕራፍ ሦስት ከአንቀጽ 13 እስከ 44 ያሉትን ይመለከቷል። እንደዚሁም የፍ·ብ·ሕ·ቁ· 1 እስከ 5 እና 8 እስከ 31 ከዚህ ጋር ያገናዝቧል።

17 ዳንኤል አዶኔል፣ የህፃናት መብቶችን ድንጋጌ ተግባራዊነት ለመቆጣጠር የሚረዱ መመሪያዎች፣" በሚል ርዕስ ለዓለም የህፃናት ደህንነት ጥበቃ ድረጅት የጻፉት ጥናታዊ ወረቀት፣ የመጀመርያ ረቂት፣ ያልታተመ፣ እ·ኤ·አ· 1992

4· ህፃናት በእኑጋገር፣ በአመጋገብና በፀሎት ጊዜያት ረገድ የራሳቸውን ሃይማኖት ደንቦች ለመከተል የአላቸውን መብትም ይቀበላል።[18]

በሀገራችን ያለውን ሁኔታም ስንመለከት በድንጋጌው ለህፃናት የተሠጡት እነዚህ መብቶች በሥራ ላይ ካሉት ሕግጋትና የመንግሥት ፖሊሲዎች ጋር ሲገናዘቡ ችግር ያለባቸው አይደሉም። ዳሩ ግን በሁላችንም ዘንድ ግልፅ በሆኑ ምክንያቶች የድንጋጌውን መርሆዎች በእለት ተእለት ሕይወታችን ከምናስተውላቸው ማኅበራዊ እውነታዎች ጋር ስናጣጥማቸው በርካታ ችግሮች ከፊታችን ተጋርጠው እንደሚገኙ በቀላሉ እንገነዘባለን።

## 2·4· <u>የሕፃናት ጥቅምና ደህንነት</u>

ሕፃናት "በአካል በአእምሮ በሥነ ምግባርና በማኅበራዊ ሕይወታቸው ዳብረውና በል ጽገው በተደላደለና ጤናማ አካባቢ ያድጉ ዘንድ" እነርሱን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች በሚቀረጹበትና ሕጎችም በሚወጡበት ጊዜ ከሁሉም በፊት ለጥቅምና ደህንነታቸው ቅድሚያ መስጠት እንደሚገባው እ·ኤ·አ· በ1959 የወጣው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የህፃናት መብቶች መግለጫ አንቀጽ 2 ያስገነዝባል። የድንጋጌው አንቀጽ 3 ከዚህም አልፎ በመሄድ ለህፃናት ጥቅምና ደህንነት መሠጠት ስለሚገባው ትኩረት የሚከተለውን ያስቀምጣል።

> ህፃናትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ መንግሥታዊ ወይም የግል የማኅበራዊ ደህንነት ተቋሞች፣ ፍርድ ቤቶች፣ የአስተዳደር ባለሥልጣኖች፣ ወይም የሕግ አውጭ አካላት እርምጃዎች ሲወስዱ የሕፃናት ጥቅምና ደህንነት ከማንኛውም ቅድሚያ ይሰጣቸዋል።

ከዚህ ጋር ተቀራራቢ የሆኑ ሃሳቦች በሌሎች በርካታ የድንጋጌው አናቅጽ ውስጥም ይገኛሉ። አንቀጽ 18 ጉዳዩን ከወላጆች ሀላፊነት አኳያ ይመለከተዋል። አንቀጽ 20 ከቤተሰቡ ተለይቶ በማደግ ላይ ላለ ሕፃን መደረግ ስለሚገባው ልዩ ጥበቃና ክብካቤ ያወሳል። በአንቀጽ 21 እንደተገለጸው ጉዲፈቻ በሚደረግበት ጊዜ ግምት ውስጥ የሚገባው ዋናው ጉዳይ ጉዲፈቻ የሚደረገው ለልጁ ጥቅምና ደህንነት መሆኑ ነው። እንደዚሁም የመዘዋወር መብቱን ያጣ እሥረኛ ሕፃን ለራሱ ደህንነት የሚጠቅም ካልሆነ በቀር ከአዋቂዎች መለየት እንዳለበት በአንቀጽ 37/ሐ/ ተደንግጓል።

ይህም ቢሆን ታዲያ "የሕፃናት ደህንነትና ጥቅም" የሚለው ሐረግ ትርጉም አልፎ አልፎ አለመግባባት ማስነሳቱ የማይቀር ነው። ለዚህ ሐረግ የሚሠጠው ትርጉም እንደየአካባቢውና እንደየሕብረተሰቡ እሴቶች የተለያየ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ለዚህ ሐረግ የሚሰጠው ትርጉም ቀኖናዊ በሆነ መልኩ ሳይሆን የሕፃናትን ደህንነትና ብልፅግና በተመለከተ ለሚከሰቱ ተጨባጭ ችግሮች ተግባራዊ መፍትሔ በሚያስገኝ መልኩ ሊሆን ይገባል። በአፅንኦት ሊስተዋል የሚገባው ጉዳይም የምንወስዳቸው አስተዳደራዊ፣ ሕጋዊና ፍትሐዊ እርምጃዎች ሁሉ ቀጥሎ ከተቀመጠው መሪ ሀሳብ ጋር መጣጣማቸውን ማረጋገጥ ነው።

---

18 ዝኒ ከማሁ

> በአንድ ሕፃንና በአንድ አዋቂ ሰው ጥቅም መሀል ግጭት በሚነሳበት ጊዜ፣ ይህን የጥቅም ግጭትም ለማስታረቅ የምንወስደው ምንም አማራጭ በማናገኝበት ጊዜ፣ በሚወሰደው እርምጃም ከሁለቱ የአንዱ ጥቅም የሚጎዳ በሚሆንበት ጊዜ፣ ለህፃኑ ጥቅም ቅድሚያ ልንሠጥ ይገባል።[19]

ከጥቂት አመታት በፊት ሸዋ ውስጥ በሚገኙ አምስት ከተሞች ይህን ጉዳይ አስመልክቶ በተደረገ ጥናት የፍርድ ቤት ዳኞች ዐቃቤያን ሕግ፣ የማኅበራዊ አገልግሎት ሠራተኞች፣ መምህራንና የቀበሌ[20] የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ከዚህ በላይ በተቀመጠው መሪ ሀሳብ ላይ አስተያየት እንዲሠጡ ተጋብዘው ነበር። የከፊሎቹ ምላሽ አወንታዊ፣ የተቀሩት ደግሞ አሉታዊ ነበር። አንዳንዶቹ ደግሞ ጭርሱኑ የሠጡት ምላሽ አልነበረም። አወንታዊ ምላሽ እንደሠጡት ተጠያቂዎች አባባል ከሆነ ለህፃኑና ለአዋቂው ጥቅም የሚበጅ የጋራ መፍትሔ ማግኘት ባልተቻለበት ጊዜ የህፃኑን ጥቅም ማስቀደሙ የሚመረጥ ነው። አሉታዊ ምላሽ የሠጡት ዳኞችና የማኅበራዊ አገልግሎት ሠራተኞች ደግሞ ከዚህ የተለየ ሀሳብ ነው ያላቸው። ለአብነት ያህል አንድ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ የሚከተለውን ምላሽ ነበር የሠጡት።

> በእኔ አስተሳሰብ የጥቅም ግጭቱ መወገድ የሚገባው ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ነው። ስለዚህም "ለህፃኑ ጥቅም ቅድሚያ ይሠጥ" የሚለውን መርህ በበኩሌ አልስማማበትም።[21]

ዳሩ ግን የህፃናት መብቶች ድንጋጌ ኢትዮጵያ ውስጥ ከመጽደቁ ከሠላሳ ዓመት በፊት የወጡት ባህረ ሕጎቻችን የሕፃናትን መብትና ደህንነት የሚመለከቱ በርካታ ደንቦችንና አስተሳሰቦችን በውስጣቸው እንዳካተቱ እንረዳለን። ለምሳሌ የመጀመሪያውን የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር ስናይ የሰው ልጅ ከልደት እስከሞት የመብት ባለቤት መሆኑን እንደሚቀበል ነው የምንረዳው። ሁለተኛው ቁጥር ደግሞ ከዚህም አልፎ በመሄድ የተፀነሰ ልጅም ቢሆን ለራሱ ጥቅም አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ እንደተወለደ የሚቆጠር መሆኑን ያመለክታል። በአወራረስ ሕግም የአንድ የተፀነሰ ልጅ አባት በሚሞትበት ጊዜ የውርስ ክፍፍሉ የልጁን መወለድ መጠበቅ እንዳለበት ተደንግጓል። ሌላ የሕግ አንቀጽ ደግሞ አንድ ሰው ኑዛዜ ካደረገ በኋላ ልጅ የወለደ እንደሆነ የዚህን ልጅ መብት ለመጠበቅ ሲባል ኑዛዜው ውድቅ እንደሚደረግ ይናገራል።[22]

የህፃናትን አጠባበቅ አስመልክቶ እያንዳንዱ ሕፃን አሳዳጊ ሊኖረው እንደሚገባ ሕጉ ያመለክታል። የገንዘብ አስተዳደርን በተመለከተ የህፃኑ መብት የሚጠበቀው በሞግዚቱ አማካይነት ነው።[23] ለህፃኑ ጥቅምና ደህንነት ሲባል የተለየ እርምጃ መውሰድ ካላስፈለገ

---

19 ዝኒ ከማሁ

20 ኢትዮጵያ ውስጥ ቀበሌ ዝቅተኛው ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ አሀድ ነው።

21 ጥላሁን ተሾመ፣ ደስታ አስፋውና ታደለ መንገሻ፣ በኢትዮጵያ የህፃናት መብቶች ሁኔታ ዘገባ፣ ለአፍሪካ ህፃናት ደህንነት ጥበቃና ጥቃት ተከላከይ ማኅበር የኢትዮጵያ ቅርንጫፍ አ.አ.አ. በጀንዋሪ 1994 በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተጠናቅሮ የቀረበ ያልታተመ ጽሑፍ፣ ክፍል ሦስት፣ ንዑስ ክፍል 1.5፣

22 የፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1063/2/፣3/፣ እና ቁ. 904፣

በቀር ይህን ተግባር የሚያከናውኑት ወላጆች ናቸው። ከሁለት ጀንዳቸው በሕይወት የሌለ እንደሆነ ወይም ተግባሩን ለማከናወን የማይቻለው በሚሆንበት ጊዜ ሌላኛው ወገን ሀላፊነቱን ለብቻው ይሸከማል። በፍርድ ቤት አሠራርም ይኸው ልምድ ተደጋፊነት አለው። በአንድ ወቅት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀርቦ በነበረ ጉዳይ የቤተ ዘመድ ጉባኤ የልጆቹ አባት በሞተበት ጊዜ የሞግዚትነትና የአሳዳሪነት ሥልጣኑን እናትየዋ እያለች ለአንድ የዝምድና ሐረጉን እንኳ በቅጡ ለይቶ ማስቀመጥ ላልቻለ ለሌላ ሰው ሠጠው። የቤተ ዘመድ ጉባኤው እናትየዋ ሞግዚት መሆን አይገባትም ባለበት ጊዜ የሠጠው ምክንያት በቂ ልምድ የላትም የሚል ነበር። የጠቅላይ ፍርድ ቤት የእናትየዋን ተቃውሞ በመቀበል ይህን የጉባኤውን ውሳኔ በሻረበት ጊዜ እንዲህ ሲል ተችቶ ነበር።

> ሕጉ በሕይወት ላለው ወላጅ የሞግዚትነትና የንብረት አስተዳዳሪነት ቅድሚያ የሠጠው ያለምክንያት አይደለም። ለልጁ ከሁሉም በፊት በሕይወት ያለው ወላጅ ቅርበት ያለውና አሳቢ መሆኑን በመረዳት ነው። ይህንን ግምት ለማፍረስ ዳኞች ጥብቅ የሆነ ጥንቃቄ ያድርጉ መባሉም የል ጆቹን ጥቅም እቁጥር ውስጥ ለማግባት ነው።[24]

ሁለቱም ወላጆች ለልጆቻቸው ሞግዚትና አሳዳሪ በኑዛዜ ሳይሰይሙ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው ከሆነ፣ አለበለዝያም በተለያዩ ምክንያቶች ወላጆቹ ይህን ኣላፊነት የማይወጡ መሆናቸው የታወቀ እንደሆነ፣ ሌሎች የቤተ ዘመድ አባላት ሞግዚትና አሳዳሪ መሆን እንደሚችሉ ሕጉ ያመለክታል። ቅደም ተከተሉም በዝምድናው ቅርበትና ርቀት ላይ የተመሠረተ ይሆናል። ይሁንና ለህፃናቱ ጥቅምና ደህንነት ሲባል ይህን ተርታ መከተል አስፈላጊ በማይሆንበቅ ጊዜ ማንኛውም ዘመድ ቢሆን የሞግዚትና የአሳዳሪነት ሃላፊነቱ እንዲሠጠው ለመጠየቅ ይችላል።

ከዚህ በላይ በተመለከቱት መንገዶች ሞግዚትና አሳዳሪ እንዲሆን የተሰየመው ሰው ለሕፃኑ ተገቢውን ጥበቃ ያላደረገ እንደሆነና በተለይም ህፃኑ

፡

> "…ለኑሮው አስፈላጊውን ጥበቃ ሳያገኝ ወይም ከግብረገብነት ጋራ የተመሳሰለ ከአእምሮው አስተዳደግ ወይም ከችሎታው ጋር የተመዛዘነ ትምህርት…ወይም ወንጀል መሥራቱ የተረጋገጠ ሲሆንና ይህም ቅጣት የደረሰበት በመጥፎ አስተዳደረግ ወይም በአሳዳሪው ጉድለት ተገቢውን የግብረ ገብነት ሥልጣኔ ለማግኘት ካለመቻሉ የተነሳ የሆነ እንደሆነ…[25]

ከዚህ ሀላፊነቱ በዳኞች ሊወገድ እንደሚችል ሕጉ ይገልጻል። እንደዚሁም በሞግዚትና አሳዳሪው ሰው ጥቅምና በህፃኑ ጥቅም መሀል ግጭት መኖሩ ሲረጋገጥ፣ የፍትሐ ብሔር ተግባሮችን ለማከናወን የማይገባ ነው፣ ወይም ዕዳ መክፈል የማይችል

---

23 የፍ·ብ·ሕ·ቁ·204 እስከ 240 ይመልከቱ። እንዲሁም የሕገመንግሥቱን አንቀጽ 36(1)(ለ) እና (2)ይመለከቷል፣

24 የፍትሐ ብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 649/82፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ያልታተመ።

25 የፍ·ብ·ቁ· 230፣ 231

ነው ተብሎ በፍርድ ሲወሰንበት፣ አለበለዝያም የሕፃኑን መብት ለመጠበቅ ሲባል በቤተ ዘመድ ጉባኤ የተላለፈውን ውሳኔ ከማስፈጸም ቸል በሚልበት ጊዜ፣ ከሀላፊነቱ ሲወገድ ይችላል።

ወላጆች በመሀከላቸው የነበረውን ጋብቻ በፍች በሚያፈርሱበት ጊዜ ከዚህ ጋብቻ የተወለዱት ሕፃናት አጠባበቅና አያያዝ ጉዳይን በተመለከተ የሚሠጥ ውሳኔ የሀፃናቱን ምቾትና ጥቅም መሠረት ያደረገ ሲሆን እንደሚገባው ሕጉ ያስገነዝባል።[26] ሕጉ ከሞላ ጎደል በተሻለ ሁኔታ ተግባራዊ በሚደረግባቸው በከተሞች አካባቢ ያለውን ልምድ ስንመለከትም የቤተ ዘመድ ግልግል ጉባኤ[27] አባላት በዚህ ረገድ ውሳኔ በሚሠጡበት ጊዜ የልጆችን ምርጫ፣ የወላጆችን የግል ሥነ ምግባር፣ የፍቺ ሀላፊነትን፣ በገንዘብ በመኖሪያ አካባቢና በትምህርት ረገድ ሀፃናቱ የሚጠብቋቸውን ዕድሎች እቁጥር በማስገባት ከወላጆቹ የትኛው ወገን የሀፃናቱን የሞግዚትነትና የአሳዳሪነት ተግባር ማከናወን እንዳለበት ሲወስኑ ይስተዋላሉ።

የሀፃናት ጥቅምና ደህንነት እፅንኦት ያገኘበት ሌላው ጉዳይ ደግሞ የጉዲፈቻ አሠራር ነው። ጉዲፈቻ የሚደረገው "...ትክክለኛ ምክንያት ሲኖርና ጉዲፈቻ ለሚደረገው ልጅ ጥቅም ያለው ሆኖ ሲታይ ብቻ ነው" በማለት ነው ይህንን ጉዳይ የሚመለከተው ሕግ የሚደነግገው።[28] ማንኛውም የጉዲፈቻ አፈጻጸም ጉዲፈቻ ከሚደረገው ሕፃን ምቾትና ደህንነት አኳያ ብቻ መታየት ይኖርበታል የሚለው የድንጋጌው አንቀጽ 21 ከዚህ ከሕጋችን አነጋገር ጋር የሚቀራረብ ነው። ይኸው አመለካከት በአዲስ አበባ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በተሠጠ አንድ ውሳኔ በሚከተለው አይነት ተንፀባርቆ ነበር። "የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ የጉዲፈቻ ወላጆች የሚሆኑ ሰዎችን ዜግነት በሚመለከት ምንም ገደብ አልደነገገም። ግምት ውስጥ የሚገባው ዐቢይ ነገር ጉዲፈቻው ለልጁ ጥቅም የሚያስገኝ መሆኑ ነው"[29]

ይህ ውሳኔ የተሠጠው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አንድ ኢትዮጵያዊ ሕፃን በውጭ ሀገር ሰዎች ጉዲፈቻ መደረጉ የሚያስገኘው የጎላ ጥቅም የለም ተብሎ ጉዲፈቻውን ውድቅ በማድረግ በተሠጠ ውሳኔ ላይ በቀረበ ይግባኝ ነበር።[30]

---

26 የፍ·ብ·ሕ·ቁ· 681፣ 682

27 የቤተ ዘመድ የግልግል ጉባኤ የፍች ክርክርን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የተሠጠው አካል ነው። የፍ·ብ·ሕ·ቁ· 666 እስከ 696 ይመለከቷል።

28 የፍ·ብ·ሕ·ቁ 805፣

29 የፍትሐ ብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 270/58፣ የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት 3ኛ ቮልዩም ቁጥር 2፣ ገጽ 422 እስከ 424፣ ይህ ውሳኔ የተሠጠው ድንጋጌው በኢትዮጵያ ከመጽደቁ ከ25 ዓመታት በፊት መሆኑን ልብ ይሏል።

30 የፍ·ብ·ሕ·ቁ· 804፣

"1· የጉዲፈቻው ውል ዳኞች ካላጸኑት በቀር ውጤት የለውም፣ /አይጸናም/።

2· ዳኞቹ ውሳኔ ከመስጠታቸው በፊት ጉዲፈቻ የሚሆነው ልጅ ከአሥር ዓመት በላይ የሆነ እንደሆነ እርሱ የሚለውንና ይህን የጉዲፈቻውን ውል አስቀድሞ አሳዳጊው ያልፈቀደ እንደሆነም የአሳዳጊውን ቃል መስማት አለባቸው።"

## 2·5· የሀፃናት የማንነት መብት

የሰው ልጅ ወደዚህ ዓለም ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ በሕብረተሰብ ውስጥ በሚኖረው ግንኙነት ማንነቱ ተለይቶ መታወቅ ያስፈልገዋል። ሰውየው በሕብረተሰቡ ውስጥ ያለው ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ብሔራዊ ማንነት ተለይቶ የሚታወቀውም ይህ መብቱ ሲከበርለት ነው። በዚህ ረገድ የድንጋጌው አንቀጽ 7 የሚከተለውን ያስቀምጣል።

> ማንኛውም ሕፃን እንደተወለደ በል ደት/የክብር/መዝገብ ይመዘገባል። ከልደት ጀምሮ መጠሪያ ስምና ዜግነት የማግኘት መብት አለው።

የድንጋጌው ፈራሚ አባል ሀገሮችም በዚህ ረገድ ያለባቸውን ዓለም አቀፋዊ ግዴታ ከሀገራዊ ሕጎቻቸው ጋር የማጣጣምና በተለይም ህፃኑ ዜግነት የሌለው ሆኖ ሲገኝ ዜግነት የሚያገኝበትን ሁኔታ የማመቻቸት ሀላፊነት አለባቸው። ከዚህም በተጨማሪ የድንጋጌው ቁጥር 8 አባል ሀገሮች "…ህፃኑ ማንነቱን ለመጠበቅ ያለውን መብት ያከብራሉ፣ ዜግነቱን፣ ስሙንና በሕግ የታወቀ የቤተዘመድ ዝምድናውን የሚቀናቀኑ ሁኔታዎችን ይከላከላሉ" በማለት ያስገነዝባል።

በ1952 ዓ·ም የወጣው የፍትሐ ብሔር ሕግም ስምንና የክር መዝገብ እያያዝን የሚመለከቱ በርካታ ደንቦችን በውስጡ ያካተተ ነው። እያንዳንዱ ሰው አንድ የቤተ ዘመድ ስም፣ አንድ ወይም ብዙ የግል ስሞችና አንድ የአባት ስም ሊኖረው እንደሚገባ ይናገራል። ህፃኑ በተወለደበት አካባቢ ባለው ቀበሌ የሚሰየመው የክብር መዝገብ ሹም ልደቱን መመዝገብ እንዳለበት፣ ወላጆችም ይህንኑ ሁኔታ ልጁ በተወለደ በዘጠና ቀናት ውስጥ መግለጽ እንዳለባቸው ይደነግጋል። ይህም የመመዝገብ መብት ወላጆቹ የማይታወቁ ህፃንንም ይጨምራል። በዚህ ጊዜ የክብር መዝገብ ሹሙ ለህፃኑ ሁለት የመጀመሪያ ስሞችንና አንድ የቤት ዘመድ ስም እንዲሠጠው ያደርጋል።[31] በተመሳሳይ መንገድ ለልደት ምዝገባ ዕውቅናን የሚሠጠው በ1949 ዓ·ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግም የተወለደ ል ጃቸውን በወቅቱ በማያስመዘግቡ ወላጆች ላይ የገንዘብ መቀጮ ወይም ቀላል እሥራት እንዲወሰን የሚያደርግ አንቀጽ ይዟል።[32]

ይሁንና በሀገሪቱ ልደትን የሚመዘግቡ ተቋሞች በተሟላ መልኩ ባለመኖራቸውና የራሱ የፍትሐ ብሔር ሕጉ የመሸጋገሪያ ደንብም የክብር መዝገብ ሥርዓትን የሚመለከቱት ቁጥሮች ራሱን የቻለ ሕግ በነጋሪት ጋዜጣ እስኪወጣላቸው ተፈጻሚ አይሆኑም የሚል በመሆኑ እነዚህን እላይ የተመለከቱትን ሥርዓቶች ተግባራዊ ማድረግ አልተቻለም።[33] ሕጉ ከወጣ ከሰላሳ አምስት ዓመት በላይ ያለፈው ቢሆንም እስካሁን ድረስ ይህን ጉዳይ አስመል ክቶ የተወሰደ መንግሥታዊ እርምጃ ባለመኖሩ ደንቡ አሁንም እንደታገደ ነው። አሁን ያለውን ነባራዊ እውነታም ስንመለከት እንግዳው ነገር ሕፃናትን እንዳይመዘገቡ ማድረጉ ሳይሆን ማስመዝገቡ ነው። በጥቂት ከተሞች የሚኖሩ የተወሰኑ የሕብረተሰብ አባላት ካልሆኑ በስተቀር አብዛኛው ሕዝብ የተወለደበትን ትክክለኛ ቀን እንኳ አያውቀውም።

---

31 የፍ·ብ·ሕ·ቁ· 32 እስከ 46

32 የወ·መ·ሕ·ቁ 623

33 የፍ·ብ·ሕ·ቁ· 3361 /1/

ዜግነትን በተመለከተ ደግሞ አሁን የሚሠራው በ1923 ዓ·ም በወጣ ሕግ ነው።[34] በዚህ ሕግ መሠረት የአንድ ሕፃን ዜግነት በወላጆቹ ዜግነት ላይ የተመሠረተ ነው። የትም ቢወለድ አንድ ሰው እናቱ ወይም አባቱ ኢትዮጵያዊ ከሆኑ እሱም ኢትዮጵያዊ ይሆናል። ሌሎች ህፃናት ግን የኢትዮጵያ ዜጎች ሊሆኑ አይችልም። ኢትዮጵያ ውስጥ መወለዳቸው በዚህ ረገድ የሚያመጣው የተለየ ውጤት የለም። እርግጥ ነው የውጭ ሀገር ዜጋ የሆኑ ሰዎች በሕጉ ላይ የተቀመጡትን ጠበቅ ያሉ መስፈርት በማሟላት የኢትዮጵያ ዜግነት እንዲሠጣቸው ማመልከት ይችላሉ። ይህን የመሰለ ጥያቄ ለማቅረብ ታዲያ አመልካቹ አካለ መጠን ያደረሰ ሊሆን ይገባል። ይህም የውጭ ሀገር ዜጎች የሆኑ ህፃናትን የኢትዮጵያ ዜግነት እንዲሰጣቸው ከማመልከት ያግዳቸዋል። ከዚህም ሌላ አመልካቹ ኢትዮጵያ ውስጥ ቢያንስ ለአምስት ዓመት በቋሚነት የኖረ፣ ራሱን ለማኖር የሚያስችል ገቢ ያለው፣ አማርኛ ቋንቋ መጻፍና መናገር የሚችል እንደዚሁም በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ ያልተወሰነበት እንዲሆን ይጠበቃል።

ይኸው የ1923 ዓ·ም የዜግነት ሕግ አመልካቹ ታዋቂ ሰው መሆኑ በሚረጋገጥበት ጊዜ ወይም የተለየ ምክንያት ሲኖር መንግሥት ከዚህ በላይ የተቀመጠውን መመዘኛ የግድ መከተል እንደሌለበት ያመለክታል። ይሁንና የውጭ ሀገር ዜጋ የሆኑ ወይም ምንም ዓይነት ዜግነት የሌላቸው ሕፃናት በዚህኛውም ልዩ ሁኔታ የመጠቀም ዕድላቸው ጠባብ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ተወልደው በተለያዩ ምክንያቶች የወላጆቻቸውን ዜግነት ያላገኙ ሕፃናትንም የሚጠብቃቸው ዕድል ተመሳሳይ ነው። እንደነዚህ ያሉት ህፃናት በዓለም አቀፉ ድንጋጌ አንቀጽ 7 እንደተመለከተው ዜግነት አልባ የመሆን አደጋ ሁልጊዜም ያንዣብብባቸዋል። በኢትዮጵያ የፍርድ ውሳኔዎችን እየሰበሰቡ በወግ የመጠረዝና የማተም ልምድ ባለመኖሩ በዚህ ረገድ ያለውን ተግበራዊ አፈጻጸምም ማወቅ አዳጋች ነው።

## 3· <u>የሕፃናት መብቶች አጠባበቅ</u>

### 3·1· <u>ሕፃኑና ቤተሰቡ</u>

ቤተሰብ የሕብረተሰብ ተፈጥሯዊና ማኅበራዊ መሠረት እንደመሆኑ መጠን የሕግ ጥበቃ ከመንግሥት ማግኘት ያለበት ተቋም ነው። ይህ መብት ከሁሉም በላይ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ባወጣው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት መግለጫም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። በተመሳሳይ መልክም በዚሁ ድርጅት የወጣው ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 10፣ ጉዳዩን እንዲህ በማለት ይገልጸዋል።

> የሕብረተሰብ ተፍጥሯዊና መሠረታዊ አሀድ እንደመሆኑ መጠን ከሁሉም የሰፋ ጥበቃና ድጋፍ ለቤተሰብ ማድረግ ይገባል። ይህም ጥበቃ በተለይ ቤተሰብ በሚመሠረትበት ጊዜም ሆነ <u>ሕፃናትን</u> <u>የመንከባከብና የማስተማር ሀላፊነት በሚሸከምበት ጊዜም</u> ጭምር የበለጠ ትኩረት ማግኘት አለበት። /አጽንኦት የተጨመረ/

የሕፃናት መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 7፣9፣እና 10 እንደዚሁ ሕፃናት በቤተሰብ ክብካቤ ማደግ ያለባቸው መሆኑ፣ ለራሳቸው ጥቅምና ደህንነት የሚበጅ መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ከቤተሰቦቻቸው መነጠል እንደሌለባቸው፣ ከቤተሰብ ጋር ለመቀላቀል ሲባል ወደአገር ለመግባት ወይም ከአገር ለመውጣት በሕፃኑ ወይም በወላጆቹ የሚቀርበውን ማመልከቻ አባል ሀገሮች በቀና መንፈስ ተቀብለው አፋጣኝ ውሳኔ መስጠት እንዳለባቸው ያመለክታሉ። ወላጆች ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ሌሎች የቤተሰብ አባላትም በድንጋጌው በተሠጣቸው መብቶች ሲጠቀሙ ተገቢ አመራር ለህፃናት በመስጠትና በመቆጣጠር ረገድ ያላቸውን ሀላፊነት፣ መብትና ግዴታ አባል ሀገሮች ማክበር እንዳለባቸው በአንቀጽ 5 ተመልክቷል።

---

[34] የኢትዮጵያ የተጠቃለሉ ሕጎች፣ አንደኛ ቮልዩም፣ ገጽ 235፣ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 6·1 "ወላጆቹ/ወላጇ፣ ወይም ከወላጆቹ/ከወላጇ አንደኛቸው ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊት የሆነ/ የሆነች የኢትዮጵያ ዜጋ ነው/ናት" በማለት ይደነግጋል።

በድንጋጌው አንቀጽ 27/2/ እንደተመለከተው ሁሉ የ1952 ዓ·ም የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግም አቅምና ችሎታቸው በፈቀደ መጠን ለህፃኑ አስፈላጊ የሆኑ የኑሮ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ረገድ ቀዳሚው ሀላፊነት የወላጆች መሆኑን ያስምርበታል። ከዚህ ሀላፊነት በተጨማሪም የሕፃኑ ወላጆች ሌሎች በርካታ ተግባርና ሀላፊነቶች እንዳሉባቸውም ሕጉ ይደነግጋል። የሕፃኑን ስም የሚመርጡት እነሱ ናቸው። የመኖሪያ ሥፍራውን ይወስናሉ፣ ጤንነቱን ይከታተላሉ፣ እንቅስቃሴውን ይመራሉ፣ ማኅበራዊ ግንኙነቱን ይቆጣጠራሉ፣ የሚመጥነው ትምህርት እያገኘ የሚያድግ መሆኑን ያረጋግጣሉ፣[35] ገቢውንና ሌሎች ንብረት ነክ ጥቅሞቹን ይጠብቃሉ።

ይህም ቢሆን ታዲያ እነዚህ በድንጋጌውና በፍትሐ ብሔር ሕጉ አናቅጽ ውስጥ የሠፈሩት አጓጊና አርኪ ሀሳቦች ብዙውን ጊዜ በሀገሪቱ ካለው እውነታ ጋር ሲጣጣሙ አይስተዋሉም። በየጊዜው በሚፈራረቁት የድርቅና የፀጥታ ችግሮች የሚባባሰው ጉስቋላው የሕዝባችን የኑሮ ደረጃ በእነዚህ ሀሳቦች ተግባራዊ አፈጻጸም ላይ የተጋረጠ ትልቁ ችግር ነው። ይህ ሁኔታ አሁን ያለውን ማኅበራዊ ሁኔታ ለመጠበቅ እንኳ የማያስችሉ መሰናከሎችን ሲያስቀምጥ ይስተዋላል። በየጊዜው ቁጥሩ አሳሳቢ በሆነ ደረጃ እያደረገ የመጣው የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናት ጉዳይ የዚህ ችግር ዓይነተኛ መግለጫው ነው። በብዙ የገጠር አካባቢዎች ያለው ስዕል ደግሞ ከጐዳና ተዳዳሪዎቹም የባሰ ነው።

እስካሁን በሀገሪቱ የተፈራረቁት መንግሥታት ችግሩን ለመፍታት ፈቃደኝነት አሳይተዋል ቢባል እንኳ ሁኔታው በእነሱ አቅምና ችሎታ ላይም አስቸጋሪና ውስብስብ ተፅዕኖን ያሳድራል። የሕፃናትን መብቶች ለህዝብ ለማሳወቅና ለማስተማር የተደረገው ጥረት አጥጋቢ ነው ማለት አይቻልም። አንድ ወጥ የሆነ የቤተሰብ ምጣኔ መርሀ ግብር በሥራ ላይ ውሎ ለማየት አልታደልንም። በድንጋጌው የተመለከቱትን መብቶች ተግባራዊነት ለማረጋገጥና ለማበረታታት አባል ሀገሮች ለወላጆችና ለአሳዳጊዎች ተገቢውን እርዳታ ይሰጣሉ፣ ለዚሁ የሚበጁ ተቋሞች መመሥረታቸውንም ያረጋግጥሉ የሚለው የአንቀጽ 18 መርሀ አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ሲገናዘብ በቅርብ ጊዜ እውን የሚሆን አይመስልም።

### 3·2· ሕፃናትን መጉዳትና ችላ ማለት

እቤትም ሆነ ከቤት ውጭ ሕፃናትን መበደል፣ማጥቃት፡ ለህፃናት ተገቢውን ትኩረት አለመስጠትና በህፃናት ጉልበት ያላገባብ መጠቀም በብዙ ሕብረተሰብ ውስጥ የተለመደ አፈጻጸም ነው። ይህን አፈጻጸም ለማስቀረት የሚያስችሉ ሁኔታዎች እስካልተመቻቹ ድረስ ህፃናት ይህን በደል ለመቃወም ድምፃቸውን የሚያሰሙበት ሁኔታ የለም።

በጥቅል አነጋገር የተበደሉና የተረሱ ህፃናት የሚባሉት የሲቪል መብቶቻቸው የተጣሱባቸው፣ እንግልት የደረሰባቸው፣ ለድብደባና ኢሰብአዊ ቅጣቶች የተጋለጡ፣ ጥቅምና መብቶቻቸውን የሚጠብቅላቸው ቤተሰብ ወይም ሌላ ማኅበራዊ ተቋም ያላገኙ ሕፃናት ሁሉ ናቸው። በአንድ ሕፃን ላይ ተገቢ ያልሆነ ድርጊት መፈጸም ወይም ለአንድ ሕፃን ሊደረግለት የሚገባውን ነገር መንፈግ በአካላዊና መንፈሳዊ ዕድገቱ ላይ አሉታዊ ውጤት ማስከተሉ የማይቀር ነው። በመሆኑም አንድ አዋቂ የሆነ ሰው ህፃኑን የሚጐዳ ተግባር ከፈጸመ ወይም ለህፃኑ መፈጸም የሚገባውን ግዴታ ከመወጣት ከተቆጠበ፣ ይህም በህፃኑ ደህንነትና ጥቅም ላይ ጐጅ ውጤት ካስከተለ፣ ይህ ሰው ህፃኑን እንደበደለ ተደርጐ ይወሰዳል። የድንጋጌው አንቀጽ 19 በዚህ ረገድ አባል ሀገሮች በህፃናት ላይ የሚደርሰውን አካላዊና ሥነ ልቦናዊ በደል ለመከላከል ተገቢ ነው የሚሉዋቸውን እርምጃዎች ሁሉ መውሰድ እንዳለባቸው ያስቀምጣል።

በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥም በህፃናት ሕይወትና ደህንነት ላይ የሚፈጸሙ እንደግድያ፣ አስገድዶ መድፈር፣ ድብደባ፣ ጠለፋ፣ እንደዚሁም በህፃናት መነገድ ከፍ ያለ ቅጣት የሚያስከትሉ የወንጀል ድርጊቶች መሆናቸው ተደንግጓል። እንደወንጀሉ አፈጻጸም ክብደት ቅጣቱ ከገንዘብ መቀጮና ቀላል እሥራት እስከ ዕድሜ ልክ ፅኑ እሥራት ወይም እስከ ሞት የሚያደርስ ነው። የፍትሐ ብሔር ሀላፊነትን በተመለከተም ቢሆን ህፃናትን በመበደልና በማንገላታት ተጠያቂ የሚሆኑ ሰዎች ተግባራቸው ወይም ግድፈታቸው በሕፃኑ መብት ላይ ያደረሰውን ጉዳት ለመካስ ይገደዳሉ።የግድያ ወንጀልን የሚመለከቱት

---

[35] የፍ·ብ·ሕ·ቁ· 34፣265 እስከ 312፣

የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ አናቅጽ[36] እንደማንኛውም የሕብረተሰቡ አባል ሁሉ የህፃናትን የመኖር መብት ስለሚጠብቁ ከህፃናት መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 6 መንፈስ ጋር የሚጣጣሙ ናቸው። በቁጥር 548 ደግሞ ሕፃናትን መበደል ራሱን የቻለ ወንጀል ሆኖ በሚከተለው መልክ ተቀምጧል።

> አሥራ አምስት ዓመት ያልሞላውን ልጅ ወይም አካለመጠን ያላደረሰውን ሰው የሚጠብቅ ወይም በአላፊነት የሚያሳድግ ሰው የልጁን ሰውነት ወይም አእምሮውን ወይም የጤናውን እርምጃ እስከማበላሸት ወይም በጣም የሚያሰጋ እስከመሆን ሆነ ብሎ ከመጠን በላይ የሥራ ልጁን ችላ ያለ የጐዳ ወይም የመታ ሰው፣ ከአንድ ወር በማያንስ እሥራት ይቀጣል።

ከዚህ ከበድ ባሉ ጥፋቶች ደግሞ ከዚህ በላይ ከተቀመጠው ቅጣትም በተጨማሪ አጥፊው ካለው የሞግዚትነትና የአሳዳሪነት ሥልጣኑም ሊወገድ እንደሚችል ሕጉ ይናገራል። ይሁንና ይኸው አንቀጽ አሳዳሪው በሕፃኑ ላይ ሕጋዊና ልከኛ የሆነ ቅጣት ቢፈጽም ተጠያቂነት እንደሌለበት ያስቀምጣል። በዚሁ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 64/2/ ላይም ሚዛናዊ የሆኑና ሕፃናትን ለማረም ተብለው የሚወሰዱ ቅጣቶች በሕግ የታዘዙና የተፈቀዱ ተግባሮች ስለሆኑ በወንጀል ድርጊት ውስጥ እንደማይካተቱ ተገልጿል። አሳዳጊዎች ህፃናትን ከጥፋቶቻቸው እንዲታረሙና እንዲማሩ ቀለል ያለ አካላዊ ቅጣት መፈጸም መቻላቸው በፍትሐ ብሔር ሕግም የተፈቀደ ነው። መምህራንና የህፃነት ማሳደጊያ ቤቶች ተቆጣጣሪዎችም ሀፃናትን ለማረምና ለማስተማር ሲሉ ተመሳሳይ እርምጃዎች ቢወስዱ ተጠያቂነት የለባቸውም።[37] እርግጥ እነዚህ አናቅጽ በህፃናት አካልና አእምሮ ላይ ጉዳት የሚያመጣ ማንኛውንም አይነት ድብደባ ከሚከለክለው ከድንጋጌው አንቀጽ 19 ጋር አብረው የሚሄዱ አይደሉም።

በሀፃናት ላይ የሚደረጉ ጠለፋዎችን መዋጋት ድንጋጌው በአባል ሀገሮች ላይ ከጣላቸው የግዴታ ዓይነቶች አንዱ ነው። በአንቀጽ 35 ላይ "ለማንኛውም ዓላማ ወይም በማንኛውም መንገድ ሕፃናትን አስገድዶ በመውሰድ፣ በመሸጥ ወይም በማስተላለፍ የሚፈጸሙ ተግባሮች" ሕገ ወጥ ተደርገዋል። በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግም የዚሁ ተግባር አሳሳቢነት ሳይታይ አልታለፈም።[38] ወንጀል ፈጻሚው እስከአምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ፅኑ እሥራት ይቀጣል። የጠለፋው ተግባር የተፈጸመው በህፃኑ ጉልበት አላግባብ ለመገልገል፣ ወይም ህፃኑን ለግልሙትናና ለአመንዝራነት ለመጠቀም፣ ህፃኑን በመያዣነት ለመጠቀም ከሆነ አለበለዚያም ህፃኑ ጭካኔ በተሞላው መንገድ የተያዘ መሆኑ ከተረጋገጠ፣ በአጥፊው ላይ የሚወሰነው ቅጣት እስከ ሃያ ዓመት ፅኑ እሥራት ሊደርስ ይችላል። ጠላፊው በፍትሐ ብሔር ሕግም የሰውን ነፃነት በመጋፋት አላፊነት ሊኖርበት ስለሚችል በተበደዩ ላይ የደረሰውን የኢኮኖሚና የሕሊና ጉዳት እንዲከስ ይገደዳል።[39]

በህፃናት ላይ የሚደርሱ ወሲባዊ ጥቃቶችን መከላከል ሌላው የድንጋጌው ዐቢይ ጉዳይ ነው። በህፃናት ላይ የሚደረጉ ወሲባዊ ጥቃቶች የሚባሉት ህፃናትን ያለፍላጐታቸው በግዳጅ ወይም በማታለል የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲፈጽሙ የመገፋፋትና የማግባባት ድርጊቶች ሁሉ ናቸው። ይህንኑ በተመለከተ የድንጋጌው አንቀጽ 34 አባል ሀገሮች በዚህ ረገድ የሚፈጸሙ ማንኛውንም ጥቃቶች የመከላከል ግዴታ እንዳለባቸው የሚደነግግ ሲሆን በተለይም፣

---

36 የግድያ ወንጀልን የሚመለከቱት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ደንቦች ቁጥር 522/ከባድ የግፍ አገዳደል/፡ ቁጥር 523/ተራ የሆነ አገዳደል/፡ ቁጥር 524/ቀላል አገዳደል/፣ ቁጥር 526 /በቸል ተኝነት ሰው መግደል/ ናቸው። በቁጥር 527 ደግሞ በመወለድ ላይ ባለ ሕፃን ሕይወት ላይ የሚፈጸም ወንጀል ለየት ያለ አገዳደል ሆኖ ተመልክቷል። በዚህም እናትየዋም ሆነ በአካባቢዋ ያሉ ሰዎች በወንጀል ተጠያቂ የሚሆኑበት ሁኔታ ሠፍሯል።

37 የፍ·ብ·ሕ·ቁ· 267/2/፡ 2039 /3/፣

38 የወ·መ·ሕ·ቁ· 560

39 የፍ·ብ·ሕ·ቁ· 2042 እስከ 2044

1· ህፃናትን በማባበል ወይም በማስገደድ በሕገ-ወጥ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ተካፋይ እንዲሆኑ ማድረግን፣
2· ለብዝበዛ ዓላማ ህፃናትን በአመንዝራ ተግባር ወይም በሌላ ሕገ-ወጥ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መጠቀምን፣
3· ለብዝበዛ ዓለማ ህፃናትን ለአስነዋሪ ትርኢቶች፣ ፎቶግራፎችና ፊልሞች መጠቀምን፣

አጥብቆ ይከለክላል። ከእነዚህ መሰፈርት አንጻር የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን ስንመለከት ሕፃናትን መድፈር፣ በህፃናት ክብረ ንጽሕና ላይ የሚደረግ መድፈር፣ ሕፃናትን ለአመንዝራ ተግባር መጠቀም በፅኑ እሥራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ሆነው መቀመጣቸውን እንመለከታለን።[40] በሕግ ከተፈቀደው የጋብቻ ዕድሜ[41] በታች ያለ ሕፃን ለዚህ ዓይነቱ ተግባር ፈቃደኝነቱን መስጠት ስለማይችል ልጁ ወዶ ያደረገው ነው የሚለው የአጥፊው መከራከርያ የወንጀል ሀላፊነቱን አያወርድለትም።

ከዚህም ሌላ ለልጆቹ የሚገባውን ቀለብ የመስፈር ሀላፊነቱን ሆን ብሎ ባልተወጣ ወላጅ ላይ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ቅጣት ይጥልበታል። እንዲጠብቃቸው የተሰጡትን ልጆች በቸልተኝነት ለጉዳት ያጋለጠውን ሰውም ሕጉ የወንጀል ተጠያቂ ያደርገዋል።[42] አጥፊው ከወንጀል ቅጣት በተጨማሪም የቤተሰብ ሀላፊነቱን ሲገፋፍና ለተበዳዩም የፍትሐ ብሔር ካሣ ሊከፍል ይችላል።[43]

በአጭሩ ሕጉ ሕፃናትን የሚበድሉ ወገኖችን በዚህ ዓይን ነው የሚመለከተው። ይህም ቢሆን ታዲያ በርከት ያሉ የሕብረተሰባችን አባላት በየዕለቱ በሕፃናት ላይ የተለያዩ በደሎችን ሲያደርሱ እንመለከታለን። እቤት ውስጥም ሆነ ከቤት ውጭ ሕፃናት ይደበደባሉ፣ እንግልት ይደርስባቸዋል፣ አልፎ አልፎም የከባድ ወንጀሎች ሰለባ ይሆናሉ። በተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ምክንያቶች በወላጆቻቸው እንኳ ሳይቀር ሲገፉና ሲንገላቱ እንዲሁም ሲጣሉ ይስተዋላሉ። ሕፃናት ሴቶች ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱና ከዚያ ሲመለሱ፣ ለቤተሰቦቻቸው መልዕክት ለመላላክ ወዲያ ወዲህ ሲሉ፣ እንጨት ሲለቅሙ ወይም ውሃ ሲቀዱ ሲደፈሩና የተለያዩ እንግልቶች ሲደርሱባቸው ማየት ያልተለመደ ነገር አይደለም። ይህ በገጠርም በከተማም የሚያጋጥም እውነታ ነው። በሕፃናት ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችንና በደሎችን የሚከታተልና የሚከላከል የተጠናከረ ድርጅታዊ መዋቅር ያላቸው ተቋሞች በሀገሪቱ ውስጥ ባለመኖራቸው የተነሳ በህፃናት ላይ ከሚፈጸሙት በደሎችና ጥቃቶች አብዛኞዎቹ ሳይመዘገቡ የሚያልፉ ናቸው። አንዳንዴም በደሎቹ በማን እንደተፈጸሙ እንኳ ሳይታወቅ ያልፋሉ። በተለይም በደሉ በወላጆችና በአሳዳሪዎች በሚፈጸም ጊዜ ጠያቂ እንኳ የለባቸውም።

በሀገሪቱ ያለውን የሕፃናት ሁኔታ በተመለከተ በአፍሪካ የህፃናት ደህንነት ጥበቃና ጥቃት ተከላካይ ማኅበር የኢትዮጵያ ቅርንጫፍ ባዘጋጀው አንድ ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ እንደተመለከተው ከመስከረም ወር 1985 ዓ·ም እስከ ሰኔ ወር 1985 ዓ·ም ባሉት የአሥር ወራት ጊዜያት ብቻ 2040 የሕፃናት በደልንና ጥቃትን የሚመለከቱ ወንጀሎች የተመዘገቡ መሆናቸውን ያፖሊስ ሠራዊት ማዕከላዊ ቢሮ መግለጹ ተዘግቧል። ከዋና ዋናዎቹ መሀል በ122 ህፃናት ላይ የግድያ ወንጀል፣ በ651 ህፃናት ላይ ድብደባ፣ በ49 ሕፃናት ላይ ወሲብ-ነክ ወንጀል፣ በ84 ሕፃናት ላይ የመግደል ሙከራ ወንጀል መፈጸሙ በዚሁ ዘገባ ተወስቷል።

---

40 የወ·መ·ሕ·ቁ· 589፣ 594፣ 605፣ 606፣ 613/2/

41 የፍ·ብ·ሕ·ቁ·581 በሕግ የታወቀው የጋብቻ ዕድሜ ለልጃገረዶች 15 ሲሆን ለወንዶች 18 ነው።

42 የወ·መ·ሕ·ቁ· 626 /1/ /ሀ/

43 የፍ·ብ·ሕ·ቁ· 2052

በዚሁ ዘገባ ላይ 34 ህፃናት ተወልደው የተጣሉ መሆኑና ከእነዚሁ ውስጥ ሁለቱ መሞታቸው ተገልጿል።[44] ከአዲስ አበባ መስተዳድር ፖሊስ ኮሚሽን በተገኘ በሌላ ዘገባ ደግሞ ከሚያዝያ ወር 1985 ዓ.ም እስከ መስከረም ወር 1986 በነበረው የስድስት ወር ጊዜ ውስጥ በክልሉ 2002 ወንጀሎች በህፃናት ላይ እንደተፈጸሙ ተመልክቷል[45]

እላይ በተጠቀሰውና ለህፃናት ደህንነትና ጥበቃ ተከላካይ ማኅበር በቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ የተገለጸ አንድ ፍርድ ቤት የቀረበ ጉዳይ የችግሩን ክብደትና አሳሳቢነት ለመገንዘብ ስለሚያስችል የጽሁፉ አቅራቢዎች ባስቀመጡበት ሁኔታ እንደሚከተለው ሠፍሯል።

ከምዕራብ ሸዋ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት በተገኘው መረጃ መሠረት ተከሳሹ ቀደም ሲል በነፍስ ግድያ ወንጀል የተፈረደበት ሰው ነበር። በወንጀል የተቀጣበትን የእሥር ዓመት እሥራት ፈጽሞ እንደተለቀቀ በአካባቢው ወደሚገኝ አንድ ቃልቻ ዘንድ ይሄድና ስለወደፊት ህይወቱ መቃናት ምክር እንዲሠጠው ይጠይቀዋል። እንደተከሳሹ አባባል ቃልቻው ያነጋገረውና ዕድሉ የሚቃናው የልጃገረድ ክብረንጽህና ዓመት እስካመት በማያቋርጥ ወንዝ ዳር ከደፈረና ቀጥሎም ያችኑ ልጅ እዚያው ወንዝ ላይ አርዶ ተራምዷት የሄደ እንደሆነ ብቻ መሆኑን ይነግረዋል። ይህን ትእዛዝ ለመፈጸም ያስብና ወደአንድ ወደሚያውቃት ጠላ እየሸጠች ወደምትተዳደር ሴት ይሄዳል። እዚያም ሴትየዋን በመደጋገም ጠላ ይጋብዛትና የስካር መንፈስ እንደተሰማት ሲረዳ የአሥራ አንድ ዓመት ዕድሜ ያላትን ል ጇን አንድ ሥፍራ ዕቃ ታደርስልኛለች በማለት ይወስዳታል። በመቀጠልም ልጅቱን አንድ ወንዝ ዳር ይወስድና ቃልቻው ያለውን ሁሉ ይፈጽምባታል። አስከሬኑንም እዚያው ትቶት ስለሄደ ጅቦች ይበሉታል። ጽሁፉ በሚዘጋጅበት ጊዜ ጉዳዩ በከፍተኛው ፍ/ቤት በቀጠሮ ላይ ነበር።[46]

3.3 ህፃናትን ስለማሠራት

> አንዳንድ ወገኖች እንደሚያደርጉት የህፃናትን የሥራ ሁኔታ የሚጠብቁ ህጎችን ጠቀሜታ ማንኳሰስ፣ አለበለዚያም ድህነትንና ኃላቀርነትን ምክንያት በማድረግ ብቻ በህፃናት ላይ የሚፈጸሙ የሥራ በደሎችን ችላ ማለት፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተወገዙ አፈጻጸሞችን ልክ ናቸው ብሎ እንደመቀበል ያህል ነው።[47]

ለየሕፃናት የሥራ ሁኔታ የሚታየው ሥራው ከተያያዘበት ኢኮኖሚያዊ ክንዋኔና በዚህ ሂደት ሊፈጠሩ ከሚችሉት ማኅበራዊ ቀውሶችና ችግሮች አንጻር ነው። በዚህ ረገድ ከሁሉም በፊት ሊጤን የሚገባው ጉዳይ በሥራ ላይ የተሰማራው ሕፃን እንደማንኛውም ህፃን

---

44 ጥላሁን ተሾመና ሌሎች፣ እላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 21 የተገለጸው ዘገባ፣ ክፍል 2፣ ንዑስ ክፍል 2.2

45 ዝኒ ከማሁ፣ ከዘገባው ጋር የተያያዘውን አባሪ ይመለከቷል።

46 ዝኒ ከማሁ፣ ክፍል 2፣ ንዑስ ክፍል 2.3. በነገራችን ላይ ጥናታዊ ጽሁፉ የተዘጋጀው በጥር ወር 1986 ዓ.ም ነበር።

47 እ.ኤ.አ. በ1983 የዓለም የሥራ ድርጅት ኮንፍራንስ ሲከፈት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ካሰሙት ንግግር የተወሰደ። አሰፋ በቀለ "Child Labour Questions and Answers" በሚል ርዕስ ካዘጋጁትና Child Labour A Briefing Manual በሚለው የዓለም የሥራ ድርጅት ዘገባ ውስጥ እ.ኤ.አ. በ1987 የታተመ።

የተለያዩ ፍላጎቶች ያሉትና ጥበቃም የሚያስፈልገው መሆኑ ነው። አካላዊና መንፈሳዊ ሰብዕናውን ለማሳደግ ሁኔታዎች ሊመቻቹለት የሚገባው መሆኑ ነው። በመሆኑም የህፃናት ሠራተኞችን ችግር መፍታት የሚደረግ ማናቸውም ጥረት ይህን ግንዛቤ በመነሻነት የጨበጠ ሊሆን ይገባዋል።

አንድ ሕፃን በኢንዱስትሪ፣ በእርሻም ሆነ በሌሎች የሥራ ዘርፎች እንዲሰማራ በሚደረግበት ጉዜና ይህም ተሳትፎው እንደህፃን ሊደረግለት ከሚገባው እንክብካቤ፣ ከአካላዊና መንፈሳዊ ዕድገቱ ጋር አብሮ የማይሄድ በሚሆንበት ጊዜ ነው ህፃኑን ለብዝበዛ ተጋልጧል የሚባለው። ህፃኑ የተሰማራበት የሥራ ባህርይ፣ ህፃኑን ላደጋ የሚያጋልጡ የሥራ ሁኔታዎች መኖር ወይም አለመኖር፣ በሥራ ላይ በመሰማራቱ ምክንያት ሊያገኛቸው ያል ቻላቸውና የወደፊት ህይወቱንና አስተዳደጉን የሚመለከቱ ሁኔታዎች ሁሉ የህፃናት ተገቢ ባልሆነ ሥራዎች ላይ መሠማራት የሚያስከትሉዋቸውን ችግሮች በመረዳት ረገድ የላቀ ጠቀሜታ ያላቸው ጠቋሚ መስፈርት ናቸው።

የችግሩን ክብደት በመረዳትም የዓለም የሥራ ድርጅት የህፃናትን ሥራ በተመለከተ በርከት ያሉ ድንጋጌዎችንና የድጋፍ አስተያየቶችን አውጥቷል። እነዚህ ድንጋጌዎች በአመዛኙ ህፃናት ወደሥራው ዓለም የሚሠማሩበትን ዝቅተኛ የዕድሜ ገደብና በተሠማሩባቸው የሥራ መስኮች ሊኖሩ የሚገቡ የሥራ ሁኔታዎችን ያመለክቱ ናቸው። በተለይም ቀደም ሲል በየጊዜው ይወጡ የነበሩ የህፃናትን የሥራ ሁኔታዎች በማጠቃለል በዚሁ ደርጅት በቁጥር 138 እ·ኤ·አ· በ1973 የታወጀው ድንጋጌ በዚህ ረገድ በዓይነተኛነት ሊጠቀስ የሚችል ነው።[48]

የዚህ ድንጋጌ አንቀጽ 2 ስለዚሁ ሲናገር ድንጋጌውን በተቀበሉ አባል ሀገሮች ውስጥና በእነዚሁ ሀገሮች በተመዘገቡ የመጓጓዣ ንብረቶች ላይ በሥራ የሚሠማሩ ህፃናት ዕድሜ ቢያንስ ቢያንስ በዚያ ሀገር በሕግ የተደነገገውን የመማሪያ ዕድሜ መጠበቅ እንዳለበት፣ በየትኛውም መልኩ ቢሆን ይህ የዕድሜ ገደብ ከአስራ አምስት ዓመት ሊበልጥ እንደማይገባው ያመለክታል። እንደ ልዩ ሁኔታ በማየት ደግሞ ብሔራዊ ኢኮኖሚያቸው በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኙ ሀገሮች ከአሠሪዎችና ከሠራተኞች ድርጅቶች ጋር በመወያየት ይህን ዕድሜ በአንድ ዓመት ብቻ ዝቅ ማድረግ እንደሚችሉም ይናገራል። የሠራተኞችን ጤንነት፣ ደህንነት ወይም ሥነ ልቦናዊ አመለካከት ለአደጋ በሚያጋልጡ የሥራ ዘርፎች ግን ዝቅተኛው የዕድሜ ገደብ አሥራ ስምንት እንደሆነ የዚሁ የዓለም የሥራ ድርጅት ድንጋጌ አንቀጽ 3 ይገልጻል። እዚህም ቢሆን ታዲያ እላይ በመደበኛ የሥራ ዘርፎች ለተሰማሩ ህፃናት በተፈቀደው ዓይነት ብሔራዊ ሕጎች ዝቅተኛው ዕድሜ በሁለት ዓመት ማውረድ እንደሚችሉም ይደነግጋል።

ከዚህ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ የተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 32 በሚከተለው ዓይነት ተቀርጿል።

> እንዳይደረግባቸው፣ አደገኛ በሆነ የሥራ መስክ እንዳይሰማሩ፣ ትምህርታቸውን የሚየሰናክል፣ለጤንነታቸው፣ ለአካል አእምሮ፣ መንፈሳዊ፣ ሞራላዊና ማኅበራዊ ዕድገታቸው ተቃራኒ የሆነ ሥራ ላለመሥራት ያላቸውን የኮንቬንሽኑ አባል ሀገሮች ህፃናት የኢኮኖሚ ብዝበዛ መብት የከብራሉ።

ከዚህም ሌላ አባል ሀገሮች ሁሉ ዝቅተኛውን ወደሥራ የመሠማሪያ ዕድሜ በሕግ እንዲወስኑ፣ የህፃናትን የሥራ ሰዓቶችና የሥራ ሁኔታዎች በተመለከተ ተገቢ ደንቦችን እንዲያወጡ፣ ይህንንም ደንብ በአግባቡ በማያከብሩት ወገኖች እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን እንዲያመቻቹ በአባል ሀገሮች ላይ ግዴታን ይጥላል።

48 በዓለም የሥራ ድርጅት አማካይነት በየዓመቱ እየታተመ በሚወጣውና International Labour Conventions and Recommendations, 1919-1981 በተሰኘው ጥራዝ እ·ኤ·አ· በ1985 ጄኔቫ ውስጥ የታተመ።

ይህን አስመልክቶ በኢትዮጵያ ሕጎች ላይ ያሉትን ሁኔታዎች ስንፈትሽ ባለፈው መንግሥት የወጣው አዋጅ ቁጥር 64/1968 ሆነ አሁን በሥራ ላይ ያለው 42/1985 ዕድሜያቸው ከአሥራ አራት ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት በሥራ ላአዋጅ ቁጥር ይ መሠማራት የሌለባቸው መሆኑን እንደሚደነግጉ እናያለን።[49] የዓለም የሥራ ድርጅትን ድንጋጌ ቁጥጥር 138 መርሆዎች በመቀበልም ህፃናት በተለይ አደገኛ በሆኑ የሥራ መስኮች መሠማራት እንደሌለባቸው አሁን በሥራ ላይ ያለው ሕግ ይደነግጋል።[50] ይህም ክልከላ የሚከተሉትን ይጨምራል።

1· አድካሚ በሆነ መንገድ መንገደኞችንና ዕቃዎችን በማጓጓዝ ሥራ ላይ፥

2· ከኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችና የማከፋፈያ ጣቢያዎች ጋር ግንኙነት ያለው ሥራ፣

3· ከመሬት በታች በሚካሄዱ የማዕድን ሥራዎች፣ የድንጋይ ካባዎችና የመሳሰሉት ሥራዎች፣

4፡ በቆሻሻ ማስተላለፍያ ቦዮችና የዋሻ ቁፋሮ ሥራዎች፣
ከዚህም በተጨማሪ ይኸው አዋጅ ቁጥር 42/1985 የህፃናት የሥራ ሠዓቶች መደበኛው በቀን ከሰባት ሰዓት መብለጥ እንደሌለበት ያመለክታል።[51]

እነዚህን በሕጉ ላይ የተቀመጡትን መስፈርት በመጠቀም በኢትዮጵያ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ስንመርምረው ግን ከዚህ በላይ ያየናቸው ዓላማዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ገቢራዊ ይሆናሉ ብለን ለመቀበል ይቸግረናል። እርግጥ ነው አሁን የተንሠራፋውን የሥራ አጥነት ችግር እንደምናየው ከሆነ የኢንዱስትሪውን ዘርፍ ወደሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ የሚጋብዙ ሁኔታዎች የሉም። ከዚያ ውጭ መደበኛ ባልሆኑ የሥራ ዘርፎች የተሰማራውን የሰው ኃይል ስንመለከት ግን እጅግ በርካታ ህፃናት ዕድሜያቸው በማይፈቅድላቸው ሥራዎች መሠማራታቸውን እናስተውላለን።

የገጠሩን ሁኔታ ስንፈትሽም ዕድሜያቸው አምስትና ከዚያም በላይ ከሆኑት ህፃናት ውስጥ አብዛኛዎቹ በእርሻና በከብት ጥበቃ ሥራ ላይ መሰማራታቸውን እናያለን። ብዙዎቹም ከቅርብ ቤተሰቦቻቸው ጋር በመተጋገዝና በመደጋገፍ ለጋራ ሕይወታቸው በሚጠቅም ሥራ ላይ የተሰማሩ እንደመሆናቸው መጠን ለኢኮኖሚያዊ ብዝበዛ ተዳርገዋል የሚባሉ አይደሉም። ይሁንና ሁኔታው በርካታ ጊዜያቸውን የሚወስድ በመሆኑ በመማር ዕድላቸውና ትምህርታቸውን በአግባቡ ለመከታተልና ለማጥናት ሊያውሉት በሚገባቸው ጊዜ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ አይቀሬ ነው።

በተከሞች ያለው ሁኔታም ከዚህ አይለይም። ቁጥራቸው እጅግ ብዙ የሆኑ ህፃናት በቤት ሠራተኝነት፣ በልጅ አሳዳጊነትና በተላላኪነት ሥራ ሲጠመዱ ማየት የተለመደ ነገር ነው። ከፊሎቹም በሊስትሮነት፣ በመኪና አጣቢነት፣ በሱቅ በደረቴነት፣ በታክሲ ወያላነትና

---

49 የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 64/1968፣ አንቀጽ 30/1/ 25/1/፣ ነጋሪት ጋዜጣ 35ኛ ዓመት ቁጥር 11 እንደዚሁም የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 42/1985 አንቀጽ 89/2/፣ 48፣ነጋሪት ጋዜጣ 52ኛ ዓመት፣ ቁጥር 27፣

50 እላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 48፣ የተገለጸውን ድንጋጌ አንቀጽ 3/2/ እና 7/1/ ይመለከቷል።

51 አዋጅ ቁጥር 42/1985፣ አንቀጽ 89/3/ /4/፣ 90፣

በሌሎችም መስኮች ተሰማርተው ይገኛሉ። እጅግ አሳሳቢ በሆነ መንገድ እያደገ ባለው የጎዳና ተዳዳሪነት[52] የተሰማሩትን ሳይጨምር ህፃናት ወላጆችና አሳዳጊዎች ጉዳዩን በቸልተኝነት ያልፉታል፣ አንዳንዴም በህፃናቱ የእነዚህ በተለያዩ ዘርፎች በሥራ ላይ የተሰማሩ ጉልበት የተሠራው ሥራ ባስገኘው ገቢ ይጠቀማሉ። ይህም የሚሆነው አንዳንድ ወገኖች ሊሉ እንደሚሞክሩት ወላጆችና አሳዳጊዎች ህፃናት በሥራ ላይ ቢሰማሩ የሚያገኙት ጥቅም በረዥሙ ህይወታቸው ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ባለመገንዘባቸው ሳይሆን፣ ልጆቹን በአግባቡ መግቦ፣ አልብሶና አስተምሮ የማሳደግ አቅሙ ስለሌላቸው ነው።

እ·ኤ·አ· በ1992 ይፋ በሆነው በብሔራዊ የህፃናትና የሴቶች ፖሊሲ ጠቋሚ ሰነድ ላይም ይኸው ችግር ሳይወሳ አልታለፈም። በዚህ ሰነድ ላይ የጎዳና ተዳዳሪዎችን ጨምሮ በሥራ ላይ የተሠማሩት ህፃናት ቁጥር ከጠቅላላው ህፃናት 78% እንደሆነ ተገምቷል።[53]

## 3·4· የሕፃናት የወንጀል አላፊነትና የወጣት ጥፋተኞች አያያዝ

ዘመናዊ የፍትሕ አስተዳደር ሥርዓት ወንጀል በሚፈጽሙ ሰዎች ላይ ክስ በሚመሠርትበት ጊዜ ህፃናትንና አዋቂዎችን በአንድ ዓይን አይመለከታቸውም። ቢያንስ በሦስት መሠረታዊ ጉዳች ላይ ይህ ልዩነት በግልጽ ይታያል። እነዚህም፤

1· የወንጀል ተጠያቂነትን በመወሰን ረገድ

2· የክሱ ሂደት፣ በሚታይበት ጊዜ ተፈጻሚ በሚሆነው የሥነ ሥርዓት ሕግ፣ እና

3· በቅጣት አወሳሰን ተፈጻሚ በሚሆነው አሠራር፣ ላይ በግልጽ ይንጸባረቃሉ፣ የወንጀል ድርጊት ፈጽሟል ተብሎ እጥፊ በተሰኘው ሰው ላይ የሚተላለፉት ውሳኔዎችና የሚወሰዱት የቅጣት እርምጃዎችም በአመዛኙ በተከሳሹ የወንጀል አላፊነት ላይ የተመሠረቱ ናቸው። በሕጉ የወንጀል አላፊነት የሚባለውም አንድ ተከሳሽ የሚሠራው ሥራ የሚያስከትለውን ውጤት በመረዳት ረገድ ካለው ብቃት ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው።

ከዚህ አኳያ ከዘጠኝ ዓመት በታች ያሉ ህፃናት የቱንም ያህል የከበደ ወንጀል ቢፈጽሙ አላፊነት እንደሌለባቸው ሕጉ ይናገራል። የእርምት እርምጃዎች ሊወሰዱባቸው የሚችሉት የቤተሰብ አባሎቻቸው፣ አሳዳጊዎቻቸው ወይም መምህራኖቻቸው ብቻ ናቸው።[54] ይህን የሚመለከተው የሕጉ አንቀጽ በድንጋጌው አንቀጽ 40/3//4/ ከሠፈረውና በአባል ሀገሮች ላይ "ወንጀል ለመፈጸም ችሎታ የለውም የሚባል ህፃንን ከፍተኛ ዕድሜ" በመወሰን ረገድ ግዴታ ከሚጥለው ደንብ ጋር የተጣጣመ ነው። በዘጠኝና በአሥራ አምስት ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ግን ለሚፈጽሙት ተግባር የወንጀል አላፊነት አለባቸው። ይሁንና በቅጣት አወሳሰን ረገድ በእነዚህ ወጣቶችና በአዋቂዎች ላይ የሚፈጸመው ደንብ የተለያየ ነው። ከአዋቂ እሥረኞች ጋርም በአንድ ክፍል መታሰር እንደሌለባቸው ሕጉ ይከለክላል። እነዚህ ወገኖች በተለምዶ ወጣት አጥፊዎች የሚባሉት

---

52 ዓለም አቀፍ የህፃናት ዓመትን ምክንያት በማድረግ እ·ኤ·አ· በ1979 አዲስ አበባ ውስጥ በተካሄደ አውደጥናት ላይ በቀረበ አንድ ጽሁፍ የከተማው የጎዳና ተዳዳሪዎች ቁጥር 3,000 እንደነበር ተገልጾ ነበር። እ·ኤ·አ· በ1994 በተካሄደ ሌላ ጥናት ይኸው ቁጥር ወደ 30,000 ማደጉን የሚጠቁሙ ምልክቶች መገኘታቸው ተዘግቧል። ይህም ቁጥሩ አሥር እጥፍ እንደጨመረ ያመለክታል። አላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 21 የተገለጸውን ሥራ ክፍል 3፣ ንዑስ ክፍል 2·4 ይመልከቱ። እንደዚሁም "National Plan of Action (Draft) for children and women 1993-2000" በሚል እ·ኤ·አ· በ1992 የወጣውን የፖሊሲ አቅጣጫ ጠቋሚ ጽሁፍ አብረው ያገናዝቡ።

53 ዝኒ ከማሁ፣ ክፍል 3፣ ንዑስ ክፍል 2·5፣

54 የወ·መ·ሕ·ቁ· 48፣ ከቁ·52 ጋር ያገናዝቧል።

ሲሆኑ ክስ ሲመሠረትባቸው ተፈጻሚ የሚሆኑባቸውን ሥርዓቶች ዝቅ ብለን እንመለከታለን።[55]

በሦስተኛ ደረጃ የሚገኙት ደግሞ ዕድሜያቸው ከአሥራ አምስት እስከ አሥራ ስምንት የሆነ ወጣቶች ሲሆኑ ለሚፈጽሙት ተግባር ሙሉ በሚሉ የወንጀል ሀላፊነት አለባቸው። የሚከሰሱትም ሆነ የሚቀጡት በመደበኛዎቹ የወንጀል ሕጎች መሠረት ነው። ይሁንና ጥፋተኛ ከተባሉ በኋላ የዕድሜያቸውን ለጋነት ለቅጣት ማቅለያነት ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ከዚህም ሌላ የቱንም ያህል የከበደ ወንጀል ቢፈጽምም በጊዜው ዕድሜው አሥራ ስምንት ዓመት ባልሞላው ወጣት ላይ የሞት ፍርድ እንደማይወሰንበት ሕጉ ይናገራል።[56] ይህም አንቀጽ በህፃናት ላይ የሞት ፍርድና የመፈታት ዕድል የሌለው የዕድሜ ልክ እሥራት እንዳይወሰንባቸው ከሚከለክለው ከዓለም አቀፉ ድንጋጌ አንቀጽ 37/1/ ጋር የተጣጣመ ነው።

የወጣት ጥፋተኞችን ጉዳይ ስንመረምር ከአላፊነት ቀጥሎ የሚመጣው ዐቢይ ነጥብ የእነዚህ ወጣቶች ጉዳይ የሚታይበት መድረክ ጥያቄ ነው። እነዚህም ለየት ባለ ሥርዓት የሚመሩ የወጣት አጥፊዎች ጉዳዮች የሚታዩባቸው ፍርድ ቤቶች ናቸው። ከዚህም ጋር አብሮ የሚታየው ሌላ ጉዳይ እነዚህ ፍርድ ቤቶች የሚመሩባቸውን ደንቦች የማውጣትና አጥፊዎቹ የሚታረሙባቸውን መዋቅሮች የመዘርጋቱ ተግባር ነው።

ይህንን ችግር በሚገባ በመገንዘብ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ የወጣት አጥፊዎች ጉዳዮች የሚታዩበትን የመነሻ ደንብ እ·ኤ·አ· በኖቬምበር 29 ቀን 1985 አውጥቷል።[57] ይህ ደንብ እልፎ አልፎ "የቤጂንግ ደንብ" እየተባለ የሚታወቀው ነው። ይህ ደንብ ወጣት አጥፊዎች የሚዳኙባቸውን መሠረተ ሀሳቦች፣ የምርመራና የክስ አቀራረብ ሥርዓቶች፣ ክርክሩ የሚያልፍባቸውን ሂደቶች፣ ሊወሰዱ የሚገቡ የቅጣት እርምጃዎች፣ በሌሎች ተቋሞች በዚህ ረገድ መከናወን ያለባቸውን ተግባሮች፣ እንደዚሁም የወጣት ጥፋተኝነትን ችግር ከሥሩ ለመቅረፍ መደረግ ያለበትን የጥናት፣ የምርምር፣ የፖሊሲ ቀረጻና የአፈጻጸም ጉዳዮች የሚዘረዝር ነው።

ከዚህም በተጨማሪ ኮንቬንሽኑ የሕፃናት የክስ ሂደት የሚታይባቸውን ለየት ያሉ አሠራሮችን፣ ህፃናት ከአዋቂዎች ጋር መታሰር የሌለባቸው መሆኑን የሚያመለክቱ ደንቦችን፣ ህፃናት እሥረኞች ከቤተሰቦቻቸው ጋር ሊገናኙ የሚችሉባቸውን ጉዳዮች የሚመለከቱ ደንቦችን አካትቶ የያዘ ነው። ሕጎች ወደኋላ ተመልሰው መሥራት አይገባቸውም፣ ማንም ሰው ሁሉ ንፁህ ሆኖ የመገመት መብት አለው፣ የተከሰሰ ሰው የክሱን ጉዳይ በይፋ ማወቅ ይኖርበታል፣ ማንም ሰው ራሱን እንዲወነጅል ሊደረግ አይገባም፣ የሚሉትና ይግባኝን የሚመለከቱት መሠረታዊ የወንጀል ክስ ሂደት መርሆዎችም በድንጋጌው አንቀጽ 40 ላይ በግልጽ ሠፍረዋል።

የኢትዮጵያ የፍትሕ አስተዳደር ሥርዓትን የሚመለከቱት ሕጎችም እነዚህን መሠረታዊ ጉዳዮች ያቀፉ ናቸው። የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ የወጣት ጥፋተኞች የክስ ሂደት የሚሰማበትን ልዩ ሥርዓት የሚወስኑ አናቅጽ ያሉት ሲሆን የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉም ተፈጻሚ የሚሆኑትን የቅጣትና የእርማት እርምጃዎች ይዘረዝራል።[58] ምንም እንኳ በወጣት አጥፊዎቹም ሆነ በአዋቂዎቹ ተከሳሾች ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑት ደንቦች አንድ ዓይነት ቢሆኑም የክስ አመራሩና የቅጣት አወሳሰኑ ሥርዓት የተለያየ ነው። የወጣት አጥፊዎቹ ክስ ሲታይ ጥብቅ የሆነውን የክርክር ሥርዓት ሁልጊዜ መከተል ግድ አይሆንም።

---

55 የወ·መ·ሕ·ቁ·53

56 የወ·መ·ሕ·ቁ· 56፣118፣

57 የወንጀል መከላከልንና የወንጀለኞች አያያዝን አስመልክቶ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በሚላኖ ከተማ እ·ኤ·አ· ከኦገስት 26 እስከ ሴፕቴምበር 6 ቀን 1985 ባካሄደው ሰባተኛ ኮንግሬስ ተደግፎ በድርጅቱ ጠቅላላ ጉበኤ በቁጥር 40/33 የፀደቀ ውሳኔ ነው። እላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 1· በተመለከተው ሥራ ውስጥ የሚገኝ ነው።

58 የወ·መ·ሕ·ቁ·161 እስከ 182

አስፈላጊ ሲሆንና በክርክሩ ሂደት ሊነሱ የሚችሉ አንዳንድ ጉዳዮችን ወጣት አጥፊው መስማት የሌለበት መሆኑ ሲታመንበት ተሰሳሹን ከችሎቱ ማግለልም ይቻላል።[59]

ወጣቱ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ፍርድ ቤቱ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የተመለከቱትን የቅጣት እርምጃዎች መውሰድ ይችላል። እነዚህ እርምጃዎች እንደነገሩ ሁኔታ አጥፊውን በጠባይ ማረምያ ተቋም እንዲቆይ ማድረግን፣ ጠበቅ ባለ ቁጥጥር ሥር ሆኖ ትምህርቱን እንዲቀጥል ማደርግን፣ ተግሣፅን፣ በቤት ማቆየትን፣ ወዘተ፣ ይጨምራሉ። እነዚህ እርምጃዎች የሚፈለገውን ውጤት ካላስገኙ ፍርድ ቤቱ ለጥፋቱ ተመዛዛኝ የሆነ የገንዘብ ቅጣት ሊወስንበት ይችላል። አጥፊው አሁንም የማይመለስ ሲሆንና ፍርድ ቤቱም አስፈላጊነቱን ሲያምንበት የአካል ቅጣት እንዲፈጸምበኄ ትእዛዝ የመስጠት ሥልጣን አለው። ይህም ቢሆን ተፈጻሚ የሚሆነው በጤናማ ሁኔታ ላይ በሚገኙ ወንዶች ወጣቶች ላይ ብቻ ሲሆን ከአሥራ ሁለት የአለንጋ ግርፋት መብለጥ እንደሌለበት ሕጉ ያስቀምጣል። እጅግ የተለየ ሁኔታ መኖሩ ሲረጋገጥና ወጣቱ ያጠፋው ጥፋት ካሥር ዓመት በሚበልጥ ጽኑ እሥራት የሚያስቀጣው ሲሆን በመደበኛ ወህኒ ቤት ታስሮ እንዲቆይ ሊደረግ ይቻላል።[60]

ከፍ ብለን የተመለከትናቸው እነዚህ የሕግ አናቅጽ ሕጉ በወጣት አጥፊዎችና በአዋቂ አጥፊዎች መሀል በክስ ሂደትና በቅጣት አወሳሰን ረገድ ለመከተል የወሰደውን የፖሊሲ አማራጭና ይህም አማራጭ ወጣት ጥፋተኞችን በቀጥታ ከመቅጣት ይልቅ ሊያስተምሩ የሚችሉ እርምጃዎችን በመውሰድ የተሻለ ውጤት የሚገኝበት መሆኑን የሚጠቁሙ ናቸው። ይሁንና የእነዚህ ዓላማዎች ተግባራዊ አፈጻጸም ባለው ድርጅታዊና መዋቅራዊ ጥንካሬ ላይ የሚመሠረት መሆኑ አያከራክረም። ከሃምሳ ሚሊዮን መብለጡ በይፋ ለሚነገርለት ሕዝብ አገልግሎት እየሠጠ ያለው የወጣት ጥፋተኞች ፍርድ ቤት አንድ ብቻ ሲሆን የሱም አቅም እጅግ ውሱን ነው። ፍርድ ቤቱ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ያልተመለከተ በመሆኑም ሕጋዊ አቋሙ ራሱ አከራካሪ ነው ከቅርብ ዓመታት በፊት አንድ ወጣት በዘረፋ ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ከተባለ በኋላ ለሁለት ዓመት ጠባይ ማረምያ እንዲቆይ ተፈርዶበት ነበር። በዚህ ፍርድ ላይ ለከፍተኛውና ለጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ቅሬታውን ባቀረበ ጊዜ ጥፋተኛው ያነሳው ክርክር ወጣት ጥፋተኞች ፍርድ ቤት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ የማይታወቅ ስለሆነ የተሠጠው ፍርድ ሕጋዊነት የለውም የሚል ነበር። ይሁንና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህን የክርክር ነጥብ ውድቅ በማድረግ የወጣት ጥፈተኞች ፍርድ ቤት የሠጠውን ፍርድ አጽድቋል። ፍርዱን በሠጠበት ጊዜ ያሠፈረው ምክንያትም ምንም እንኳ የወጣት ጥፋተኞች ፍርድ ቤት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ያል ተመለከተ ቢሆንም በተግባር ግን የወጣት አጥፊዎችን ጉዳዮች እያየ ለረዥም ዘመናት ሲወሰን የቆየ ስለሆነ በዚህ ረገድ የዳኝነት ሥልጣንም የለውም ብሎ መከራከር አግባብ አይደለም የሚል ነበር።[61]

በመደበኛ ፍርድ ቤቶችም ዳኞች የወጣት ጥፋተኞችን ጉዳዮች በሚመለከቱበት ጊዜ በተከሳሽነት የቀረቡትን ወጣቶች የግል ሥነ ምግባርና ቀደም ሲል የነበረውን ታሪክ ለማወቅና ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት እንዲችሉ ተገቢ ነው የሚሉትን ግለሰብ ወይም ተቋም መረጃ የመጠየቅ ሥልጣን እንዳላቸው ሕጉ ይደነግጋል። ዳሩ ግን ከፖሊስ አካላት በስተቀር ይህን መሰል መረጃ ሊሠጡ የሚችሉ ተቋማትና ወገኖች የሉም። ትምህርት ቤቶች በዚህ ረገድ ጠቀሜታ ሊኖራቸው ይችላል። ይሁንና ይህም ቢሆን በቂ ነው የሚባል አይደለም። ትምህርት ቤቶቹ ራሳቸው የየግል ችግሮች አሉባቸው፣ በበርካታ የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥም ቁጥራቸው ብዙ የሆኑ ህፃናት የመማር ዕድል አያገኙም። በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የተገለጹት የማረሚያና የማሻሻያ ተቋሞች፣ አዲስ አበባ ውስጥ ካለው ጠባይ ማረሚያ በቀር፣ ገና በሀሳብ ላይ ያሉ ናቸው። አለ የሚባለው ተቋምም ከጥቂት መቶ ወጣቶች በላይ የመቀበል አቅም የለውም። በየጊዜው በተለያዩ አካባቢዎች የሚቋቋሙት ወህኒ ቤቶች ለወጣት ጥፋተኞች የተለዩ ክፍሎች የሚያዘጋጁ ስለመሆኑ ቢያንስ በዚህ ጸሐፊ አይታወቅም።[62]

---

59 ይህን ጉዳይ በተመለከተ የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘት፣ ስታሊን ዜድ ፊሸር፣ "የወጣት ጥፋተኞች፤ የወንጀል ክስ ሥነ ሥርዓት"፣ በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት 7ኛ ቮል ዩም ቅጽ 1 ከገጽ 115–173 ያሳተሙትን ጥናታዊ ጽሁፍ ይመልከቱ።

60 የወ·መ·ሕ·ቁ· 173 (1)(ሀ) እና (ለ)

61 የወንጀል መዝገብ ቁጥር 1027/81፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ያልታተመ፣

የወጣት አጥፊዎች ጉዳይ ግን በየጊዜው አሳሳቢነቱ እየጨመረ በመምጣቱ ከፍተኛ ትኩረት የሚያሻው ነው። ከፖሊስ ወንጀል ምርመራ የተገኘው የሚቀጥለው መረጃ የጉዳዩን ከባድነት የበለጠ ለመረዳት ጠቃሚ ነው።

> ከመስከረም እስከ ሰኔ ወር 1983 ዓ·ም ባሉት የአሥር ወር ጊዜያት 5477 ወጣት አጥፊዎች ተመዝግበዋል። ከእነዚህ ውስጥ 457 በነፍስ ግድያ /6·5%/፣ 1153 በድብደባ /21%/፣ 1898 በስርቆት /34·66%/፣ 24 አደገኛ ዕፅ በማዘዋወር /1·04%/፣ ሌሎችም ተመዝግበዋል።[63]

ብዙዎቹ የወንጀል ተግባሮች በፖሊስም ጭምር ሳይታወቁ የሚያልፉ በመሆናቸው ምክንያት ከዚህ በላይ ያለው አኀዝ ትክክለኛውን ስዕል ሙሉ በሙሉ የማያሳይ መሆኑን ፖሊስ ራሱም ይቀበላል።

## 4· ማጠቃለያ

በርከት ያሉት የሀገራችን ሕግጋት የህፃናትን መብቶች የሚመለከቱ አናቅጽ የያዙ ሲሆኑ አንዳንዶቹም በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ያየናቸው ናቸው። ሕገ መንግሥቱም የተለያዩትን የህፃናት መብቶች የሚያመለክት ራሱን የቻለ አንቀጽ የያዘ ነው።[64] በአንቀጹ የተካተቱት ጉዳዮችም የሕፃናት መብትን በተመለከተ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ካገኙ መርሆዎች የተወሰዱ ናቸው።

ይህ አበረታች እርምጃ መሆኑ አያነጋግርም። ዳሩ ግን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ላወጣው የህፃናት መብቶች ድንጋጌ መርሆዎች ተግባራዊነት ያለን ቁርጠኝነት ከቃላት ባሻገርም መሄድ የሚገባው ነውና በዚህም እቅጣጫ ገና ብዙ መሥራት ይኖርብናል።

---

62 የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 36(3) እንዲህ ይላል "ወጣት አጥፊዎች በማረሚያ ወይም በመቋቋሚያ ተቋሞች የሚገኙ በመንግሥት እርዳታ የሚያድጉ ወጣቶች በመንግሥት ወይም በግል እጓለ ማውታን ተቋሞች ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ከአዋቂዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው"

63 እላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 21 የተገለጸው ሥራ፣ ክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል 1·8፣

64 ሕገ መንግሥት፣ አንቀጽ 36፣